ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ-ሙስና

ፀረ–ሙስና ቅጽ 1 ቁጥር 5 ኅዳር 2015 ዓ.ም

# የፀረ-ሙስና ብሔራዊ ኮሚቴ ተቋቁሞ ወደ ስራ መግባቱ ተገለፀ

ሙስና ሀገርን የሚበላ ነቀዝ ሲሆን፣ የሀገርን አንጡራ ሀብት እየቦረቦረ ጥሪቷን ባዶ ለማስቀረት ሌት ተቀን የሚማስን ተባይ ነው። ዋልጌ ባለሥልጣናት፣ በፍቅረ ነዋይ የታወሩ ደላሎች እና ባለሃብቶች አንድ ላይ ሲገጥሙ፤ ከነዚህ የሌብነት ፊታውራሪዎች ጀርባ ብዛት ያላቸው ዜጎች መሰለፍ ሲጀምሩ ሙስና የተባለው ነቀዝ ሀገርን እንደ ወረርሽኝ ያጠቃታል።

ሙስና በየትኛው ቦታና በየትኛውም ዘመን ሊኖር ይችላል፤ ነገር ግን የሀገርን ልማት አጥንቱ ድረስ እስከ መጋጥ ከደረሰ ሙስና አንድ አደገኛ ወረርሽኝ ሆኗል ማለት ነው። ሙስና ሀገርን ሊያፈርስ የሚችል የደኅንነት ሥጋት መሆኑን ያስመሰከሩ ሀገሮችን በዘመናችን አይተናል። የአደንዛዥ ዕጽ፣ የኮንትሮባንድ፣ ሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር፣ ሕገ ወጥ የጦር መሣሪያ ንግድ፣ የንግድ ማጭበርበር ሙስናን ለዓላማቸው ማስፈጸሚያነት ይፈልጉታል። በዓለማችን የተጀመሩ ጦርነቶች እንዳይጠናቀቁ፤ ግጭቶች እንዳይበርዱ፣ ሕዝቦች እርስ በርስ እንዲጋጩ፣ ከሚያደርጓቸው ምክንያቶች አንዱ ሙሰኞች ከዚህ አይነት ቀውሶች ስለሚያተርፉ ነው።

ሙስና ዛሬ የሀገራችን የደኅንነት ሥጋት ሆኗል፤ ወደ ብልጽግና የምናደርገውን ጉዞ እጅ ተወርች አሥሮ ለመያዝ ከጠላቶቻች እኩል ሙሰኛው እየታገለን ነው። የተስተካከለ ቢሮክራሲ፣ የተቀናጀ መዋቅርና ዘመናዊ አሠራር ለሙስና ተጋላጭነትን ስለሚቀንሱ፣ እነዚህን ለማጥፋት ወይም ለማሰናከል ሙሰኛው ቀን ከሌት እየሠራ ነው። ሕዝባችን በአገልግሎት አሰጣጥ፣ ከመሬት ጋር በተያያዙ አሠራሮች፣ በፋይናንስ ዘርፍ፣ በሽያጭና ግዥ ሂደቶች፣ በፍትሕ አደባባዮች፣ በተለያዩ የመንግስት ተቋማት፣ የልማት ድርጅቶች፣ የህዝብ ተቋማት ወዘተ. በሚያጋጥመው ሙስና እየተማረረ ነው። በተለያዩ ጊዜያት ከሕዝብ ጋር በተደረጉ ውይይቶች ከጸጥታ ሥጋቶች እኩል ሙስና የብልጽግና ጉዟችን ዋናው ዕንቅፋት መሆኑን አንሥቷል።



መንግሥት በየደረጃው የሚገኘውን መዋቅር በመፈተሽ፣ አዳዲስ አሠራሮችን በመዘርጋት፣ በቴክኖሎጂ የታገዙ ሥራዎችን እያሳለጠ ሥራዎችን ከእጅ ንክኪ ነጻ በማድረግ፣ በሙስና ወንጀል የሚሳተፉ አመራሮችንና ሌሎች ተዋንያንን ለሕግ በማቅረብ፣ ሙስና ምቹ ሁኔታ እንዳይፈጠርለት ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል። ነገር ግን ሀገራችን ያጋጠማትን ጦርነትና

የፀረ-ሙስና ... ወደ ገጽ 2 የዞረ



“በተደራጀ ሌብነትና ሙስና ላይ የተጀመረው እርምጃ ሀገርን ከዘረፋ የማዳን ህዝባዊ ትግል ነው” - የኮሚሽኑ ኮሚሽነር ሳሙኤል ኡርቃቶ (ዶ/ር)

ገጽ 2

ሙስና እና ብልሹ አሠራር የዕድገታችን ነቀርሳ በመሆኑ ልንታገለው ይገባል ተባለ

ገጽ 5

ኮሚሽኑ ሀገር አቀፍ የፀረ-መስና ኮሚሽኖች ትስስር 7ኛ ጉባኤ አካሄደ

ገጽ 5

# የአማራ ክልል ዋና ኦዲተር በተቋማት ላይ ባደረገው ኦዲት የተገኙ ክፍተቶችን ለማረም አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ ተጠየቀ

የአማራ ክልል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት በ12 የተመረጡ ተቋማት ላይ ባደረገው ኦዲት የታዩ ክፍተቶችን ለማረም አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ የክልሉ ምክር ቤት አባላት ጠየቁ።

የአማራ ክልል ምክር ቤት በ4ኛ መደበኛ ጉባኤው የቀረበለትን የክልሉን ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ሪፖርት መመርመር ችሏል።

የክልሉ ዋና ኦዲተር ዶ/ር አማረ ብርሀኑ ለምክር ቤቱ ባቀረቡት ሪፖርት በ12 የመንግሥት ተቋማት ላይ የክዋኔ እና የክትትል ኦዲት መደረጉን ገልጸዋል።

በኦዲቱ የሕዝብ እና የሀገር ሀብት ምዝበራ መፈፀሙን ያሚያሳዩ ግኝቶች መመላከታቸውን ለምክር ቤቱ አብራርተዋል። ከዚህም ውጪ የአሠራር ክፍተቶች መታየታቸውንም ዋና ኦዲተሩ ተናግረዋል።

ይህም የመንግሥት እና ሕዝብ ሀብት ለታለመለት ዓላማ እንዳይውል እና እንዲመዘበር አድርጓል ብለዋል።

ሪፖርቱን ያዳመጡት የምክር ቤቱ አባላትም ኦዲት ማድረግ ብቻ እንደ ግብ መታየት እንደሌለበት ገልጸው፣ በግኝቶች ላይ ተመሥርቶ ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤቱ ግፊት እንዲያደርግ እንዲሁም የክዋኔ እና ክትትል ኦዲት ሥራው ከዚህ በበለጠ ተደራሽ እንዲሆን ጠይቀዋል።

የፍትሕ ተቋማት ከዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ጋር በመቀናጀት የተመዘበረ የሀገር ሀብት እንዲመለስ በትኩረት ሊሠሩ እንደሚገባም የምክር ቤት አባላቱ አሳስበዋል።

የደብረ ታቦር ከተማ ቤቶች እና ኮንስትርክሽን፣ የአማራ ክልል ገጠር መንገድ ኮንስትራክሽን ኤጀንሲ፣ የአማራ ክልል ጤና ቢሮ፣ የፍኖተሰላም እና የእንጅባራ ከተማ አስተዳደሮች፣ መሬት ቢሮ እና የመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ልማት ቢሮ ኦዲት ከተደረጉት ተቋማት መካከል የሚጠቀሱ ናቸው ሲል የአማራ ሚዲያ ኮርፖሬት መረጃ ያመለከታል።



# "በተደራጀ ሌብነትና ሙስና ላይ የተጀመረው እርምጃ ሀገርን ከዘረፋ የማዳን ህዝባዊ ትግል ነው"- የኮሚሽኑ ኮሚሽነር ሳሙኤል ኡርቃቶ (ዶ/ር)

በተደራጀ ሌብነትና ሙስና ላይ የተጀመረው እርምጃ ሀገርን ከዘረፋ የማዳን ህዝባዊ ትግል መሆኑን የፌደራል ስነ-ምግባርና ጸረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነርና የጸረ-ሙስና ብሔራዊ ኮሚቴው አባል ዶክተር ሳሙኤል ኡርቃቶ ገለጹ።

ሙስና እና የተደራጀ ሌብነት ህዝብን ያማረሩ የመልካም አስተዳደር ችግሮች በመሆናቸው መንግስት የጉዳዩን አሳሳቢነት በመገንዘብ የጸረ-ሙስና ብሔራዊ ኮሚቴ አቋቁሞ ወደ ስራ መግባቱን ዶክተር ሳሙኤል ጠቁመዋል። በዚህም መረጃዎችና ጥቆማዎች ከእጅ ንክኪ ነጻ በሆነ መንገድ ሲሰበሰቡ መቆየታቸውን ጠቅሰው፤ እስከ አሁን ባለው ሂደት 250 መረጃዎች ተለይተው ለምርመራ ዝግጁ መሆናቸውን ተናግረዋል። ኮሚቴው የህዝብ አመኔታ ያለው አሰራር እንዲከተል ከፍተኛ ጥንቃቄ መደረጉንም ነው የገለጹት።

በሙስና እና የተደራጀ ሌብነት ላይ የተጀመረው ትግል ሁሉን አቀፍ መሆኑን የሚናገሩት ዶክተር ሳሙኤል፤ የፌዴራል ተቋማት ኃላፊዎችን ጨምሮ በሙስና የተሳተፉ አካላት ላይ ያለርህራሄ እርምጃ እንደሚወሰድ አረጋግጠዋል። በሙስና ወንጀል ተጠርጥረው በቁጥጥር ስር የዋሉት የፋይናንስና ደህንነት አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር አቶ ቴዎድሮስ በቀለንና ሌሎች የተቋማት ኃላፊዎችን በዚህ ረገድ ለአብነት አንስተዋል።

መንግስት የጀመረው የጸረ-ሙስና ትግል ሀገርን ከዘረፋ የማዳንና ብሔራዊ ደህንነቷን የማረጋገጥ ስራ መሆኑን ጠቅሰው፤ ከዚህ አኳያ ትግሉ ህዝባዊ መሆኑን መገንዘበ ይገባል ብለዋል። ሙሰኞች ለፍርድ ቀርበው ሀገር የምታጣውን ሀብት ማዳን የሁሉም ዜጎች ኃላፊነት መሆኑን መገንዘብ እንደሚገባም አመላክተዋል።

ኅብረተሰቡ በየጊዜው በሙሰኞች ላይ አስተማሪ እርምጃ እንዲወሰድ ሲጠይቅ መቆየቱን ያስታወሱት ኮሚሽነሩ፤ የኮሚቴው መቋቋም ለህዝብ ጥያቄው ምላሽ የሚሰጥ መሆኑን ተናግረዋል። በመሆኑም ኮሚቴው በቀጣይ በተደራጁ የሙስና ወንጀል ተጠርጣሪ ግለሰቦች ከወንጀል ተጠያቂነት ባሻገር በሙስና ያፈሩት ሀብት እንዲወረስ፣ ያሸሹትም እንዲመለስ ይሰራል ብለዋል።

የጸረ-ሙስና ትግሉ የአንድ ወቅት ዘመቻ ብቻ ሳይሆን ተቋማዊ አደረጃጀትን በመያዝ ተጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑንም ኮሚሽነሩ ዶክተር ሳሙኤል አመላክተዋል።

የኢትዮጵያ የሙስና ሁኔታ ምን ላይ እንደሚገኝ ባለፉት ሁለት ዓመታት ጥናት መደረጉን ጠቅሰው፤ ችግሩ ብሔራዊ ስጋት መሆኑ ታውቋል ብለዋል። የሙስና ወንጀል በኢትዮጵያ ከድህነት፣ ከኑሮ ውድነትና ሥራ አጥነት በመቀጠል ከፍተኛ አገራዊ ችግር መሆኑ በጥናቱ መረጋገጡንም ጠቅሰዋል። በመሆኑም ይህንን የአገር አደጋና ብሔራዊ ስጋት ለመዋጋት በሚደረገው ጥረት የሕዝቡ ድጋፍና ተሳትፎ እንዲጠናከር ኮሚሽነሩ ጠይቀዋል።

የሙስና ወንጀልን መከላከል የሚቻለው በትውልድ ግንባታ በመሆኑ በስነ-ምግባር ግንባታ ላይ አተኩሮ እየተሰራ መሆኑን ጠቅሰው፤ የመከላከል ሥራውም የጋራ ጥረትን የሚጠይቅ መሆኑን ገልጸዋል።

በመንግሥት የተቋቋመው የፀረ-ሙስና ብሔራዊ ኮሚቴ ተቋማትን በማጎልበት ጉድለታቸውን እያረሙ የሙስና ወንጀልን እንዲከላከሉ ማድረግ መሆኑን ተናግረዋል። የሙስና ወንጀልን ለመከላከል በሚደረገው ጥረት ኮሚቴው ከሕዝቡ ጋር በመተባበር በቁርጠኝነት የሚሰራ መሆኑንም አረጋግጠዋል።

ከዚህ ቀደም መረጃ በተለያዩ ተቋማት ይሰበሰብ እንደነበር ያስታወሱት ዶክተር ሳሙኤል፤ አሁን ላይ ግን በብሔራዊ የመረጃ ቋት እንዲመጣ የሚደረግ መሆኑን ገልጸዋል።

የፀረ-ሙስና ትግሉ የአገር ህልውና ጉዳይ በመሆኑ ለትግሉ የሁላችንም ትብብርና እገዛ ሊታከልበት ይገባል ብለዋል። ተቋማትም ግልፅነት ማስፈን እንዳለባቸውና አመራሮች ተጠያቂነትን ለማስፈን በቁርጠኝነት መሥራት እንዳለባቸውም አመላክተዋል። የመገናኛ ብዙኃንም የፀረ-ሙስና ትግሉን በማገዝ የድርሻቸውን እንዲወጡ ኮሚሽነሩ ከኢዜያ ጋር በነበራቸው ቆይታ ጠይቀዋል።

# የፀረ-ሙስና ብሔራዊ ኮሚቴ...




ኮሮናን የመሳሰሉ ወረርሽኞች የመንግሥትን ትኩረት ወስደዋል ብለው ያሰቡ ሙሰኞች፣ በየቦታው ተሠግሥገውና ኔት ወርክ ዘርግተው፣ ኢትዮጵያን ለማጥፋት እየሠሩ መሆናቸውን በዝርዝር የቀረበው የጥናት ሪፖርት ያሳያል። መንግሥት በጸጥታው ዘርፍ እንዳደረገው ሁሉ በሙስና ላይ ጠንካራና የማያዳግም ኦፐሬሽን ማድረግ እንዳለበት የጥናቱ ውጤትና የሕዝብ ውይይቱ ግምገማ ያመለክታል። በአንድ በኩል የመንግሥት ሕጎች፣ደንቦች፣ መመሪያዎችና አሠራሮች ለሙስና ያላቸውን ተጋላጭነት የማጥፋት ሥራ ይሠራል፤ በሌላ በኩል ደግሞ የሙስና ተዋንያንን የማጋለጥና በሕግ የመጠየቅ ተግባር ይከናወናል።

መንግሥት በጥናት በደረሰባቸው የመንግሥት ሹመኞች፣ የመንግስት ተቋማት ሰራተኞች፣ አቀባባዮችና ጉቦ ሰጪዎች ላይ ምርመራ እያደረገ ይገኛል። ነገር ግን ሙስና በባሕርዩ በረቀቀ መንገድ፣ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም፣ አንዳንድ ጊዜም በሕጋዊነት ሽፋን የሚካሄድ በመሆኑ በመንግሥት ጥናት የተደረሰባቸው አካላትን ብቻ ለሕግ በማቅረብ የሚፈታ አይደለም። ሙስናን ከሥር ከመሠረቱ ለመንቀል እንዲቻል ከሕግና ከአሠራር ማሻሻያዎች በተጨማሪ፣ የሙስና ተዋንያን ሁሉ ሙስናን እርም እንዲሉ የሚያደርግ ርምጃ ያስፈልጋል።

መንግሥት በሙስና ላይ የሚያደርገውን ዘመቻ የሚያስተባብር፣ በጥናት ተለይተው ከቀረቡት በተጨማሪ ሌሎችንም ተዋንያን የሚለይና ለሕግ እንዲቀርቡ የሚያደርግ ብሔራዊ ኮሚቴ አቋቁሟል።

ብሔራዊ ከሚቴው ሰባት አባላት ያሉት ሲሆን፣ እነርሱም፡-

1. አቶ ተመስገን ጥሩነህ
2. ዶ/ር ጌዴዎን ጢሞቴዎስ
3. አቶ ተክለ ወልድ አጥናፉ
4. አቶ ሰሎሞን ሶቃ
5. አቶ ደበሌ ቃበታ
6. ዶ/ር ሳሙኤል ኡርቃቶ
7. አቶ አብዱሃሚድ መሃመድ ናቸው።

ይህ የፀረ-ሙስና ብሔራዊ ኮሚቴ የተሰጠውን ኃላፊነት በብቃት ለመወጣትና ትርጉም ያለው ውጤት ለማምጣት እንዲችል የኅብረተሰቡ ሙሉ ትብብር እጅግ አስፈላጊ ነው። ኅብረተሰቡ በሙስና ላይ በሚደረገው ዘመቻ ሊሳተፍ እንደሚገባ በተለያዩ መድረኮች ሲያነሣ ቆይቷል። መንግሥትም ይሄንን የሕዝብ ተሳትፎ በእጅጉ ይፈልገዋል፤ ምክንያቱም ሙስና በዋናነት የሚጠፋው ሕዝብ አምርሮ ሲታገለው ነውና።

በመሆኑም ኅብረተሰቡ የሙስና ተዋንያንን በተመለከተ ያለውን መረጃ፣ ከቂምና ከበቀል ነጻ በሆነ መንገድ፣ ይፋ በሆኑት አድራሻዎች ለብሔራዊ ኮሚቴው በመላክ ሙስናን ለማጥፋት በሚደረገው ትግል ንቁ ተሳታፊ እንዲሆን ጥሪ የቀረበ ሲሆን፣ የሚቀርቡ ጥቆማዎች የጠቋሚዎችን ደህንነት ለማረጋገጥ ተገቢውን ጥንቃቄ እና ሚስጥራዊነት በጠበቀ መንገድ ተይዘው ይመረመራሉ።

በተያያዘ መረጃ መንግስት ብሄራዊ ኮሚቴው የሚወስዳቸው እርምጃዎች እና የእንቅስቃሴው ውጤት በየጊዜው ለህዝብ ይፋ ይደረጋል በተባለው መሰረት ብሄራዊ ኮሚቴው በሰጠው መግለጫ የመሬትና የመንግስት ቤቶች አስተዳደር፣ የፀጥታና የፍትህ ዘርፍ፣ የፋይናንስ ዘርፍ፣ የመንግስት ገቢና ጉምሩክ ስርአት እንዲሁም የአገልግሎት አሰጣጥ፣ አስተዳደርና የመንግስት ግዢ ዘርፎች ላይ ትኩረት አድርጓል።

ቀድሞ በተደረጉ ማጣራቶች በወንጀሉ የተጠረጠሩትን የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር አቶ ቴዎድሮስ በቀለን ጨምሮ በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር፣ በብሄራዊ ደህንነት አገልግሎት ውስጥ በተለያየ ደረጃ ያሉ የስራ ሃላፊዎች፣ ፖሊስ፣ ዐቃቤ ህግና ዳኞች በቁጥጥር ስር ውለው ማጣራት እየተደረገባቸው ነው።

ተጠርጥረው ከሃገር የሸሹ ግለሰቦችንም ወደ ህግ ለማቅረብ ከተለያዩ ሃገራት ጋር ወንጀለኛን አሳልፎ የመስጠት ስምምነቶች ሲፈፀሙ መቆየታቸውንም አስታውሷል።

በአዲስ አበባም የአርሶ አደር ልጆች ወይም የልማት ተነሺ ሳይሆኑ የሆኑ በማስመሰል በሐሰት ሙስና የሰሩ ግለሰቦችም ተለይተዋል ብለዋል የብሔራዊ ኮሚቴው አባል ዶ/ር ጌዲዮን ጢሞቲዎስ። 175 ሺህ ካሬ ሜትር ቦታና የኮንዶሚኒየም ቤት ምዝበራ የፈፀሙ እንዲሁም በፍትህ ዘርፉ ስልጣናቸውን በመጠቀም ከግለሰቦችና ከንግድ ተቋማት ጋር ለግል ጥቅማቸው ሲሰሩ የነበሩ ተጠርጣሪዎችም ተለይተዋል ተብሏል።

ኮሚቴው ሶስት ንዑስ ኮሚቴዎችን ማለትም የህግ፣ የመረጃ እና የፋይናንስ ንዑስ ኮሚቴዎችን በማቋቋም እቅድ አውጥቶ ስራ መጀመሩንም የብሔራዊ ኮሚቴው ሰብሳቢና የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር አቶ ተመስገን ጥሩነህ ተናግረዋል።

በመንግሥት አግልሎት አሰጣጥ፣ በፋይናንስና ግዥ፣ በፍትህ ስርዓቱ እና በመሬት አስተዳደር እንዲሁም በመሰረታዊ ፍጆታ አቅርቦት ዘርፎች ላይ ሙስና በከፍተኛ ሁኔታ ይስተዋላል ብለዋል።

የሌባ ትንሽ የለውም ያሉት አቶ ተመስገን ጥሩነህ፤ ከመታወቂያ አሰጣጥ ጀምሮ ህብረተሰቡን የሚያማርሩት ላይ ጠንካራ እርምጃ ይወሰዳል ብለዋል።

ብሄራዊ ኮሚቴው በተቋቋመ በአንድ ሳምንት ውስጥ ብቻ ከህብረተሰቡ ከ250 በላይ ጥቆማዎች ተሰብስበዋል ያለው መግለጫው ህብረተሰቡ በ9555 ጥቆማውን እንዲቀጥል ጥሪ ቀርቧል።

በቀላልና በጥልቅ ማጣራት እርምጃ የሚወሰድባቸው ጥቆማዎች ተለይተዋል፤ በወንጀሉ ተጠርጥረው በቁጥጥር ስር የዋሉት የስራ ሃላፊዎች ላይ ክስ ይመሰረታል ነው የተባለው።

ብሄራዊ ኮሚቴው የሚወስዳቸውን እርምጃዎች በተከታታይ ለህዝብ ይፋ እንደሚያደርግም ተመላክቷል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ ለኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 6ኛው ዙር 1ኛ አመት 4ኛ መደበኛ ጉባዔ ወቅት ለምክር ቤት አባላት ሲያብራሩ ሌብነት አታካች ነገር በመሆኑ የፍትሕ ሥርዓቱ ላይ ትልቅ ስብራት እንዳለና ሥርዓቱን ለማስተካከል የሁሉንም ተሳትፎ ይጠይቃል፤ በቴሌግራም ግሩፕ ከፍተው ገንዘብ የሚቀባበሉ የፍትሕ ሰዎች ስለመኖራቸውም እንዲሁም ሌብነት ብቻ ሳይሆን ሥራ የሚገሉ ሰዎች የሚገኙ ሲሆን፣ ይህን ለማስተካከል ሀገር ወዳድ የሆኑ አካላትን ይዞ ጠንካራ ለውጥ በፍትሕ ሥርዓቱ ማምጣት እንደሚጠበቅም ተመላክቷል።

መንግሥት 'ቀይ መስመር' ብሎ ያሰመረውን ሌብነት፣ ሌቦች 'ቀይ ምንጣፍ' እያደረጉት ነው ብለዋል። ሌብነት የኢኮኖሚ ነቀዝ እና የዕድገት ነቀርሳ ቢሆንም፣ አንዳንድ አካላት ግን ድርጊቱን እንደመብት እየወሰዱት በመሆኑ አደገኛ ሁኔታ እየተፈጠረ ሲሆን፣ በሌብነት ላይ ተጨባጭ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል ጥናት እየተደረገ መሆኑን መናገራቸው ይታወሳል።

በተመሳሳይ መረጃ በጠቅላይ ሚኒስቴር ዶ/ር አብይ አህመድ በተሰጠ አቅጣጫ መሰረት የአዲስ አበባ ከተማ እና የክልል ርእሳነ መስተዳድሮች በየደረጃው የሚሠሩ ክልላዊ የፀረ-ሙስና ኮሚቴ በማዋቀር ወደ ስራ መግባታቸውን ለመረዳት ተችሏል።

ብሔራዊ የሙስና ድርጊቶች ጥቆማ መስጫ አድራሻዎች
ስልክ: 9555
አጭር የፅሁፍ መልዕክት: 9555
ድረ ገፅ: http://www.9555pmo.et/
ኢሜይል: http://9555pmo.et/
ቴሌግራም:https://t.me/PMOfeedback

የሙስናና ብልሹ አሰራር ድርጊቶችን በጥቆማ መስጫ አድራሻዎች ያጋልጡ፣ይጠቁሙ!!

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ-ሙስና

## በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ


ስልክ 011552-77-79
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ኢ-ሜይል FeaccEthiopia2013@et
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ፌስቡክ www.facebook.com/feaccOfficial
ቴሌግራም t.me/feacc
ትዊተር www.twitter.com/EthiopiaFeacc
ዩቲዩብ Federal Ethics & Anti-Corruption Commission

**ለሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ስራዎች**
**www.feaccdars.gov.et**


## ለፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና ወንጀል ጥቆማ መስጫ አድራሻዎች


ስልክ 011552-77-92/ 011553-38-52
ሞባይል 0935947533
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ኢ-ሜይል CorruptionReportEthiopia@feacc.gov.et
ቴሌግራም t.me/CorruptionPointing
ዋትስአፕ wa.me/qr/5IGXTSIYUMPBF1


# ርዕሰ -አንቀፅ

ሙስና በአገራችን የሚከናወኑትን የልማት ሥራዎች በማደናቀፍና የተቋማትን የአገልግሎት አሠጣጥ ቀሰ በቀስ እንዲዳከሙ በማድረግ፣ የህግ የበላይነት በመሸርሸር፣ በህግ ጥበቃ የተደረገላቸውን የዲሞክራሲና ሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች እንዲጣሱ በማድረግ ሕዝባችንን በመንግስት ያለው እምነት እንዲያጣ የሚያደርግ የሁሉም የመልካም አስተዳደር ችግሮች ቁንጮ ነው። ይህ የመልካም አስተዳደር ፀር የሆነውን ወንጀል በዘላቂነት ለመከላከል ሕዝባዊ መሰረት ያለዉ፣ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች አደረጃጀቶችና ባለድርሻ አካላትን በተገቢዉ ሁኔታ ያሳተፈ የፀረ-ሙስና ትግል ሰርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል።

በዚህ መሰረት ውጤታማ እና አሳታፊ የፀረ ሙስና ትግል እንዲኖር ለማድረግ ሀገራዊ የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች የትብብር እና የትስስር ሰርዓት ተዘርግቶ ሙስና በሀገራችን ኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ላይ ሊያደርሰው የሚችለውን ሁለንተናዊ ስጋት ለመቀነስ የሚያስችል እንቅስቃሴ እየተደረገ ይገኛል። የተዘረጉ የአሰራር እና የትብብር ማዕቀፎች ተግባራዊና ውጤታማ የሚሆኑት ሁሉም በየደረጃው የሚገኙ ባላድርሻ አካላት እና ተቋማት ለህዝብ የገቡት ቃል መሰረት ሲፈፅሙ እና የተግባር ሰው ሆነው መገኘት ሲችሉ ነው። በመሆኑም የተጀመረውን ሀገራዊ የፀረ-ሙስና ትግል ተቋማዊ አደረጃጀትና አሰራር ላይ ተመስረቶ እንዲከናወን፣ ዜጎች በመንግስት ባለስልጣናትና ሰራተኞች የሚፈፀሙ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች በተጨባጭ መረጃ ላይ ተመሰርተው እንዲያጋልጡ ማድረግ የሚያስችል ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማድረግ እንዲሁም የተባላሹ አሰራሮችን ለማረም የሚያስችል አሰቀድሞ የሙስና ስጋት ጥናት ላይ የተመሰረተ የቅደመ መከላከል አሰራር በመዘርጋት የተደራጀ እና የጥቅም ትስስር የዘረጉ ምንጩ ያልታወቀ ሀብት የሚያካብቱ አካላት ፖለቲካዊ እና ህጋዊ ተጠያቂነት የሚያረጋግጥ አሰራሮች ላይ ትኩረት ያደርጋል።

ሙስና ልማትን በማዳከም የሀገርን እድገት የሚያቀጭጭ፣ የሞራልና የሥነምግባር ቀውስ እንዲባባስ፣ ሰላምና መረጋጋት እንዳይኖር የሚያደርግ፣ህዝብ በመንግስትና በህግ የበላይነት ላይ አመኔታ እንዲያጣ የሚያደረግ፣ አደገኛና ድንበር ዘለል ባህሪ ያለው አለማቀፋዊ ወንጀል ሲሆን፣ ዛሬ የሀገራችን የደኅንነት ሥጋት በመሆን ወደ ብልጽግና የምናደርገውን ጉዞ እጅ ተወርች አሥሮ ለመያዝ ከጠላቶቻችን እኩል ሙሰኛው እየታገለን ነው። የተስተካከለ ቢሮክራሲ፣ የተቀናጀ መዋቅርና ዘመናዊ አሠራር ለሙስና ተጋላጭነትን ስለሚቀንሱ፣ እነዚህን ለማጥፋት ወይም ለማሰናከል ሙሰኛው ቀን ከሌት እየሠራ በመሆኑ፣ ሕዝባችን በአገልግሎት አሰጣጥ፣ ከመሬት ጋር በተያያዙ አሠራሮች፣ በፋይናንስ ዘርፍ፣ በሽያጭና ግዥ ሂደቶች፣ በፍትሕ አደባባዮች፣ በተለያዩ የመንግስት ተቋማት፣ የልማት ድርጅቶች፣ የህዝብ ተቋማት ወዘተ. በሚያጋጥመው ሙስና እየተማረረ ነው።

ሙስናን ከሥር ከመሠረቱ ለመንቀል እንዲቻል ከሕግና ከአሠራር ማሻሻያዎች በተጨማሪ፣ የሙስና ተዋንያን ሁሉ ሙስናን እርም እንዲሉ የሚያደርግ ርምጃ ያስፈልጋል።

መንግሥት በሙስና ላይ የሚያደርገውን ዘመቻ የሚያስተባብር፣ በጥናት ተለይተው ከቀረቡት በተጨማሪ ሌሎችንም ተዋንያን የሚለይና ለሕግ እንዲቀርቡ የሚያደርግ ብሔራዊ ኮሚቴ ተቋቁሞ ሌቦችን ካሉበት አድኖ በመያዝ ላይ ይገኛል።

ስለሆነም ይህ የፀረ ሙስና ብሔራዊ ኮሚቴ የተሰጠውን ኃላፊነት በብቃት ለመወጣትና ትርጉም ያለው ውጤት ለማምጣት እንዲችል የኅብረተሰቡ ሙሉ ትብብር እጅግ አስፈላጊ ነው። ኅብረተሰቡ በሙስና ላይ በሚደረገው ዘመቻ ሊሳተፍ እንደሚገባ በተለያዩ መድረኮች ሲያነሣ ቆይቷል፤ መንግሥትም ይሄንን የሕዝብ ተሳትፎ በእጅጉ ይፈልገዋል፤ ምክንያቱም ሙስና በዋናነት የሚጠፋው ሕዝብ አምርሮ ሲታገለው ነውና።


ቀጣዩ የኢትየጵያ የፀረሙስና ትግል ምዕራፍ ሕዝባዊ መሰረት ያለዉ፣ የባድርሻ አካላት ንቁ ተሳትፎ ያረጋገጠ፣ መረጃና ዕዉቀት ላይ የተመሰረተ ከንግግር ተሻግሮ በተግባር ለዉጥ ያሳየ ሊሆን ይገባል። ይህን የዕድገት፣ የልማትና የመልካም አስተዳደር ነቀርሳ የሆነዉን ሙስና ከሥር መሰረቱ ለመንቀል ሁሉም እንደየሚናዉ ቁርጠኛ መሆን ይገባል።

በአለም 19ኛ በሀገራችን 18ኛ ጊዜ ‹ሙስናን መታገል በተግባር› በሚል መሪ ቃል ህዳር 30/2015 ዓ.ም የሚከበረው የፀረ-ሙስና ቀን መንግስት ሙስና የሀገራችን ነቀርሳ መሆኑን በመረዳት ብሄራዊ የጸረ-ሙስና ኮሚቴ አወቅሮ ሙስናን ለመታገል ቁርጠኛ በመሆን ወደ ተግባር በገባበት ወቅት መሆኑ በዓሉን ከሀገራዊ ዘመቻው ጋር በማተሳሰር ከፌደራል እስከ የወረዳ ቀበሌ ድረስ ኮሚቴ በማዋቀርና በዓሉን በደመቀ ሁኔታ በማክበር የሙስናን አስከፊነት ለህብረተሰባችን ግንዛቤ በመፍጠር ወደ ስራ የተገባበት ጊዜ በመሆኑ ለየት ያደርገዋል።

በመሆኑም ኅብረተሰቡ የሙስና ተዋንያንን በተመለከተ ያለውን መረጃ፣ ከቂም በቀል ነጻ በሆነ መንገድ፣ መንግስት ይፋ ባደረጋቸው አድራሻዎች ለብሔራዊ ኮሚቴው በመላክ እንዲሁም ካሳንችስ በሚገኘው የኮሚሽኑ ቢሮ በአካል በመገኘት መረጃ በመስጠት ሙስናን ለማጥፋት በሚደረገው ትግል ንቁ ተሳታፊ እንዲሆን ጥሪ የቀረበ ሲሆን፣ የሚቀርቡ ጥቆማዎች የጠቋሚዎችን ደህንነት ለማረጋገጥ ተገቢውን ጥንቃቄ እና ሚስጥራዊነት በጠበቀ መንገድ ተይዘው ይመረመራሉ።

# ኮሚሽኑ ከንግድ ዘርፍ ባለድርሻ አካላትና ከሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና አስፈፃሚዎች ጋር ሀገር አቀፍ ውይይት አካሄደ







ኮሚሽኑ ከ250 በላይ ከሚሆኑ ሀገር-አቀፍ ከንግድ ዘርፍ ባለድርሻ አካላት፣ ከህግ፣ ፍትህና ዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ እና ከንግድና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢዎችና አባላት፣ ከክልል የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች፣ ከሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና አስፈፃሚዎችና ከሚዲያ እንዲሁም ከባለድርሻ አካላት ጋር በዘርፉ በሚስተዋሉ የሙስና ስጋቶች ላይ በአዳማ ከተማ ኃይሌ ሪዞርት ውይይት አካሄዷል።

መድረኩን በንግግር የከፈቱት የፌዴራል ሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ሳሙኤል ኡርቃቶ (ዶ/ር) ለሙስና እና ሙሰኞች እጅ መስጠት እንደማያስፈልግ ገልጸው፣ ሙስናን ለመዋጋት ከነበረው የተለየ የህግ ማስከበር ስራ በተግባር የሚታይበት አካሄድ መኖር አለበት ብለዋል። መንግስት በተለያዩ መድረኮች እንደገለፀው ሙሰኞች ሙስና ቀይ መስመር ነው የተባለውን ወደ ቀይ ምንጣፍ ቀይረውታል፣ ስለዚህ ለሀገር ስጋት ሆኖ መቀጠል ስሌለለበት የፀረ-ሙስና ትግላችንን በአዲስ ምዕራፍ እንቀጥላለን ብለዋል።

ዶ/ር ሳሙኤል አክለውም በዘርፉ በሚስተዋሉ የሙስና ስጋቶችን ለመቅረፍና የፀረ-ሙስና ትግላችንን ለማሳለጥ ሙስናን በማጋለጥ በኩል የምርመራ ጋዜጠኞች ሚና ከፍተኛ መሆኑን፣ የመንግስት ከፍተኛ አመራሮች በተጠያቂነትና በግልፅነት ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ፣ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት አባላት ተጠያቂነትን በዘላቂነት እንዲያሰፍን ባለቤት ሆነው እንዲመሩ እንዲሁም ጠንከር ያለ ክትትልና ግምገማ በማድረግ የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና አስፈፃሚዎች ሙስናን በመከላከል፣ በማስተማርና በማጋለጥ ሚናቸውን እንዲወጡ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል። ሙሰኞችን በህግ ተጠያቂ ለማድረግ መንግስት አሁን ላይ በልዩ ትኩረት እየሰራ ነው ያሉት ኮሚሽነሩ የዚህ የትኩረት አቅጣጫ ተሳታፊ መሆን የሁሉም ኃላፊነት መሆኑን አስገንዝበዋል።

ሌላው በመድረኩ ላይ ንግግር ያደረጉት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የንግድና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ አይሻ ያህያ በሀገራችን የተጀመረው የዕድገት ጉዞ በሙስናና ብልሹ አሰራር እንዳይደናቀፍ በቅንጅት መከላከል ይገባል ያሉ ሲሆን፣ የንግድ አገልግሎቱ ግልፅነት ማጣት፣ የህገ ወጥ ንግድ፣ የገበያ አሻጥሮች፣ የህገ ወጥ ደላሎች መበራከት በንግዱ ዘርፍ የሚስታወሉ ግድፈቶች በመሆናቸው የአሰራር ስርዓት ጥናት በማድረግ ችግሩን መፍታት እንደሚገባና የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትም የበኩላቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ አሳስበዋል።

በንግድ ዘርፍ የሚስተዋሉ የሙስና ስጋቶች በተመለከተ የሥነ ምግባርና የፀረ-ሙስና ስልጠና መሪ ሥራ አስፈፃሚ በአቶ ዳግም አላምረው ገለፃ ተደርጎ ከመድረኩ ተሳታፊዎች ጋር የጋራ መደረግ ተችሏል። በዘርፍ የተሰማሩ ሌቦች የሚሰርቁት በዘመቻ ሲሆን ክትትሉ ግን በተወሰኑ ሰዎች በመሆኑ ምንም አይነት የንግድ ፍቃድ ሳይኖራቸው በብዙ ሚሊዮን ብርና ከ26 በላይ መኪና የሚያቀሳቅሱ ግለሰቦች በሞሉበት ሀገር ሌባ ሌባ ማለት ብቻ የለብንም፤ የፍትህ አካላትን ማጠናከርና ክትትል ማድረግ ቀዳሚ ተግባር መሆን አለበት የሚል ሀሳብ በተሳታፊዎች ተነስቷል።

በአሁኑ ወቅት ሌብነት በህግ የተፈቀደ እስኪመስል ድረስ ከላይ እስከ ታች በሰሰለት የተሳሰረ ሲሆን፣ አሁን ያለው አመራር በማን አለብኝበት በገገማው ለመስረቅ ፍራትና ስጋት የላቸውም ብለዋል።

የስነምግባር መከታተያ ክፍሎች ተጠሪነታቸው ለኮሚሽኑ መሆን ካልቻለ ለውጥ ማምጠት አንችልም፤ የስራ ኃላፊዎቻችን ዝም ብላችሁ ደሞዛችሁን ብሉ በማለት ሙስናን እንዳንታገል እንቅፋት እየሆኑባቸው መሆኑን በውይይቱ አብራርተዋል። የዘርፉ ባለቤት ንግድ ሚኒስቴር በመድረኩ በመገኘት የሚነሱ ችግሮችን ለይተው ግብዓት መውሰድ ነበረባቸው ብለዋል።

ም/ኮሚሽነር ወዶ አጦ በሙስናና በብልሹ አሰራር የተዋጥን በመሆኑ አጀዳዉን ብሄራዊ አድርገን ችግሩን ሁላችንም በጋራ ልንጋፈጠው ይገባል ያሉ ሲሆን፤ የህዝብ ተወካዮች አባላትም ድርሻችሁን በመውሰድ በትቂት ስግብግብ ግለሰቦች ሀገራችን ችግር ውስጥ እንድትወድቅ መፍቀድ የለብንም ብለዋል።

ኮሚሽኑ በአሁኑ ወቅት ግንዛቤ የመፍጠር እና ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን የመከላከል ስራዎችን የሚያከናውን ሲሆን፣ የክስና የምርመራ ስራው ወደ ሌላ ተቋም በመሄዱ የቅንጅት ስራ ይሰራል። ህዝባችን በአንድ በኩል የኑሮ ውድነት በሌላ በኩል ሙስናና ብልሹ አሰራር እየጨቆነው ጫንቃው እየዛለ በመሆኑ ሁላችንም በጋራ በመረባረብ ከዚህ ችግር ማውጣት ይኖርብናል በማለት ለተሳታፊዎች መልክት አስተላልፈዋል።

በጥናቱ ማጠቃለያ ላይ የተገኙት ኮሚሽነር ዶ/ር ሳሙኤል ኡርቃቶ የፌደራል የስነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር እስከ ታችኛው መዋቅር ያለውን አደረጃጀት መጀመሪያ ማፅዳት ያስፈልጋል ያሉ ሲሆን በቀጣይ በጥናቱ የተለዩ ብልሹ አሰራሮችን የማጥራት ስራ ለመስራት እርሾ የሚጥልልንና ሌባውን ከጤነኛው የምንለይበት ጊዜ ይሆናል ብለዋል።

ነፃና ገለልተኛ ለህዝብ የቆሙ ተቋም መገንባት አስፈላጊ ሲሆን፣ ሙስና የሚሰሩ ግለሰቦች አብረውን ያሉ እንጂ ከሌላ ብላኔት የመጡ አይደሉም፤ ሌቦች ከባለስልጣናት ብቻ የሚጠለጠል ሳይሆን ከሀይማኖት ተቋማት ላይም ይገኛል ብለዋል። ለሙስና ትግል ተስፋ የምናደርገው በህዝባችን ጥሩ አቋምና ፅናቱን በመመልከት ዕንጂ በንግዱ ዘርፍ የሚስተዋለው ሙስና በጣም የተወሳሰበና አስቸጋሪ ነው ያሉ ሲሆን፣ መንግስት የፖለቲካ ቁርጠኝነት በተቋማት ላይ የሚታይበት ሂደት በመጀመር የተቋማት ኃላፊዎችን ሌባ ነህ መባል ተጀምሯል፤ በቀጣይም የተሻለ ስራ የሚሰራበት ሂደት ይኖራል ብለዋል።

በቀጣይ በሃይማኖት፣ በብሄር እና በመንደር በመተሳሰር ሙስናና ብልሹ አሰራር በመሸዋወድ እየሰሩ የሚኖሩ አመራር አይኖሩንም ብለዋል። ሚድያ፣የባህል ተቋማት፣ የሀይማኖት ተቋማትና ሲቪክ ማህበራት የሌብነት አስከፊነትን ግንዛቤ በመፍጠር የበኩላቹህን አስተዋፆኦ መወጣት ይኖርባችኋል በማለት መልክት አስተላልፈዋል። ሙስናን መቀነስ የሚቻለው በወሬ ጋጋታ ሳይሆን ሁሉም አካላት በቅንጅት መስራት ሲችል ነው ብለዋል። ሀብት መዝገባን ከማንዋል በማውጣት በድጅታል የአመዘጋገብ ስልት በመቀየር ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ከተገኘ ማንም ይሁን ማንም ተመላሽ እንዲደረግና ተጠያቂነትን ማስፈን ይገባል ያሉ ሲሆን፤ ሀብት ሰውረዋል በሚል ጥቆማ ቀርቦ ትክክለኛነቱ ከተረጋገጠ ከተመለሰው ሀብት ለጠቋሚው 25 በመቶ በሽልማት ይበረከትለታል በማለት አብራርተዋል።

በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የንግድና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ ወ/ሮ አይሻ ያህያ በበኩላቸው ተጠያቂነትን በማስፈን ሙስናና ብልሹ አሰራርን በመቀነስ ትውልዱን መታደግ የሁላችን ድርሻ ነው፤ የምክር ቤት አባላትም ትኩረት ሰጣችሁ መስራት ይኖርባችል ያሉ ሲሆን፣ የመንግስት ባለስልጣናትንና የንግድ አካላት ሰርቀው ከተገኙ ተጠያቂ መደረግ አለባቸው ብለዋል።

ሙስና በምን አለብኝነት እንደሚሰራ በጥናቱ መረዳት መቻሉን ገልፀው፣ ሙስና ህዝባችን መሸከም ከማይችልበት ደረጃ ላይ ደርሷል ያሉ ሲሆን፣ ከመንግስት ተቋማ አገልግሎት ለማግኘት ብር ይዞ መሄድ ጀምሯል ብለዋል።

ምክር ቤቱ ለህዝብ ወገተኝነት በመቆም ከክልሎች ጋር በጋራ በመሆን እስከታች ድረስ የተለያዩ የግንኙነት አማራጮች በመጠቀም ህብረተሰቡ ላይ ግንዛቤ በመፍጠር እንደ ቋሚ ኮሚቴ ሙስና በመታገልና የተለያዩ የዘርፉን ተግባራት ለማከናወን ቁርጠኛ መሆን ይኖርብናል በማለት ለውይይት ተሳታፊዎች መልክት አስተላልፍል።

# በኢትዮጵያ የሥነ ምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ረቂቅ ፖሊሲ ላይ ውይይት ተካሄደ





ኮሚሽኑ በኢትዮጵያ የሥነ ምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ረቂቅ ፖሊሲ ላይ ከ35 ከሚበልጡ ከመንግስት፣ ከባለድርሻ አካላት፣ ከሚዲያ፣ ከጥበብ አካላትና ከሐይማኖት ተቋማት እንዲሁም ከሲቪል ሶሳይቲ ተሳታፊዎች ጋር ውይይት አካሄዷል።

ኮሚሽኑ በሀገራችን እየተካሄደ የሚገኘውን የፀረ-ሙስና ትግል ይበልጥ ውጤታማ ለማድረግ የሚያግዝ ሀገር አቀፍ የፀረ-ሙስና አማካሪ ካውንስል ለማቋቋም የፀረ-ሙስና ረቂቅ ፖሊሲ አዘጋጅቶ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በረቂቁ ላይ ውይይት ማድረግ ችሏል።

በፌደራል ስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን

አቶ ሀረጎት አብርሃ ረቂቅ ፖሊውን ለተወያይወች ማቅረብ ችለዋል።

በ2022 ዓ.ም ከሙስና የፀዳች ኢትዮጵያን ለመፍጠር ራዕይ ያደረገው ኮሚሽኑ ብሔራዊ ስጋት የሆነው ሙስናን ለመከላከል ይረዳ ዘንድ የእቅድ ፖሊሲዎችን በዝርዝር አቅርቧል።

በረቂቅ ፖሊሲው የተገኙ ተወያዮች ረቂቅ ፖሊሲው ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን ለመታገልና ስነምግባር ለመገባት የሚያስችል እንዲሆን የተለያዩ ገንቢ ሀሳቦችን ማንሳት ችለዋል።

የፌደራል የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶ/ር ሳሙኤል ኡርቃቶ ረቂቅ ፖሊሲውን ለባለድርሻ አካላት ማቅረብ የተፈለገው የተለያዩ ሀሳቦች ተፀባርቀው በሀገራችን ሙስናን መታገል የሚያስችልና መልካም ስነምግባርን መመገባት የሚያስችል ፖሊሲ ለማዘጋጀት ታሳቢ ያደረገ መሆኑን ለተወያዮች አብራርተዋል።

ሀገራችን ኢትዮጵያ ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን በመታገል ሙስና የአለም ብሎም የሀገራችን ዕድገት እንቅፋት እንዳይሆን ታሳቢ በማድረግ አለማቀፋዊ ስምምነቶችን ከተፈራረሞ ሀገራት አንዷ በመሆኗ በተጨባጭ ሙስናን በመታገል ወደ ሀገራችን ለሚመጡ የተለያዩ የንግድ ተቋማት ስጋት መሆን ይለባትም።

ዶ/ር ሳሙኤል ኡርቃቶ አክለውም ፖሊሲውን የሚከታተልና ሙስና በሀገር ምን ደረጃ ላይ እንደሆነ ለህዝብ ይፋ የሚያደርግ ራሱን የቻለ ምክር ቤት ማቋቋም መታሰቡን ለመድረኩ ተወያዮች ጠቁመዋል። የኢኮኖሚ አሻጥሮችን በማካሄድ የኑሮ ውድነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እንዲስፋፋ ከሚያደርጉ ዋነኛ ጉዳዮች መካከል አንዱ ሙስና በመሆኑ የሁሉም ባለድርሻ አካላትና የህዝቡ ርብርብ አስፈላጊ መሆኑም በምክክሩ ተዳሷል።

ሙስናን ለመከላከል ሚዲያዎች በምርመራ ማካሄድ እንደሚገባቸው እና የህዝብ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ላይ ልዩ ምርመራዎች ማካሄጃ መንገዶች እና ህዝቡ ካለ ስጋት ጥቆማ እንዲሰጥ የሚያስችሉ ሀሳቦች በፖሊሲው ሰነድ ተብራርቷል።

በውይይቱ የሚቋቋመው የፀረ-ሙስና አማካሪ ካውንስል በሥነ ምግባር ግንባታና በፀረ-ሙስና ትግል የሚስተዋሉ የፖሊሲና የአፈፃፀም ክፍተቶች ላይ የሚመክር መሆኑ ተጠቁሟል።

# ሙስና እና ብልሹ አሠራር የዕድገታችን ነቀርሳ በመሆኑ ልንታገለው ይገባል ተባለ

በጉቦና በተለያዩ ብልሹ አሠራሮች የሚገለፀው የሙስና ተግባርና አመለካከት በልማት፣ በመልካም አስተዳደር እና በዜጎች ፍትሃዊ ተገልጋይነት ላይ እያሳደረ ያለው ተፅዕኖ እየጨመረ መምጣቱን የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ገልጿል።

እንደ ሀገር ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ ያለውን ሙስናንና ሙሰኞችን የመታገል ተግባር ውጤታማ ለማድረግ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልልም የፀረ-ሙስና ትግሉን አጠናክሮ መቀጠሉን የክልሉ ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር አቶ መንግሥቱ ላሎ ገልፀዋል።

በአቋራጭ የመበልፀግ ፍላጎትና ግለኝነት የተጠናወታቸው አካላት ፍትሃዊ አሰራርን ወደ ጎን በመተው በጉቦ እና በጥቅማ ጥቅም በመታሰር የሰፊውን ህዝብ ፍትሃዊ ተጠቃሚነት እየጎዱ መሆኑን ያወሱት ኮሚሽነሩ፤ በክልሉ ባለድርሻ አካላትንና ማህበረሰቡን ባሳተፈ መልኩ ሙስናን ለመከላከል እየተሰራ መሆኑን አስታውቀዋል ።

የፍትህና የዴሞክራሲ ተቋማት የልማት ነቀርሳ የሆነውን ሙስናን ለመዋጋት ተግተው እንዲሰሩ የጠየቁት ኮሚሽነር መንግስቱ ላሉ፣ በተለይ የሚዲያ ተቋማት ኅብረተሰቡን ባሳተፈ መልኩ የሙስና ተግባራትን ለመከላከል የሚያስችሉ መረጃዎችን በማሰራጨት የትግሉ አካል እንዲሆኑ ጥሪ አቅርበዋል።

ህብረተሰቡም ማንኛውም ዓይነት ብልሹ አሰራር ሲመለከት ጥቆማዎችን በነፃነት በስልክ፣ በአካልና በተለያዩ አማራጮች ለኮሚሽኑ እንዲያቀርብ ጠይቀዋል።

ለዚሁ መገልገያ የሚሆን ነፃ የስልክ መስር እየተመቻቸ በመሆኑ ለህዝብ ይፋ እንደሚደረግ ኮሚሽነሩ ገልፀዋል።





በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በንግድ፣ በመሬት አስተዳደር፣ በኢንቨስትመንት እና በመሠረተ ልማት ዝርጋታ ዘርፎች ሰፊ የሙስናና ብልሹ አሰራር ተግባራት መኖራቸውን ኮሚሽኑ ባደረገው ጥናት ማረጋገጡን ኮሚሽነሩ አቶ መንግስቱ ላሎ ተናግረዋል።

በተመሳሳይ መረጃ የክልሉ የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን፣ የክልሉ ፍትሕ ቢሮ እና የክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ፣ የሙያ ፍቃድ፣ የንግድ ፍቃድና የመንጃ ፍቃድ በተመለከተ በጋራ ለመስራት የስምምነት ሰነድ ተፈራረሙ።

የክልሉ የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር መንግስቱ ላሎ በፊርማው ሥነ-ስርዓት ላይ እንዳሉት ሀሰተኛ ሰነዶችን የመለየት ሥራ በሃገር አቀፍ ደረጃ የተጀመረው የፀረ-ሙስና ትግል አንድ አካል ነው ብለዋል።

ይህም በአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ውስጥ የሚታየው የሕዝብ እሮሮ ምክንያት አገልግሎት እንዲሰጡ የተመደቡ አመራሮችና ባለሙያዎች በሐሰተኛ የትምህርት ማስረጃ የተመደቡ በመሆናቸው የሚፈለገውን አገልግሎት የመስጠት የዕውቀትና የክህሎት ክፍተት እንዳለባቸው የገለጹት ኮሚሽነር መንግስቱ ይህንን አጣርቶ እርምጃ መውሰድ የሚስተዋለውን የብልሹ አሰራር ሂደት እንደሚቀርፈው ጠቁመዋል።

የክልሉ ፍትሕ ቢሮ ም/ኃላፊ አቶ ብርሃኑ አየሁ እንዳሉት ሐሰተኛ የትምህርት ማስረጃዎች በስፋት እየተሰራጩ መሆናቸውን እና በመንግስት ተቋማት በብዛት ሊገኙ እንደሚችሉ ጠቅሰዋል። በተጨማሪም የሰራተኞች የቅጥርና የምደባ ስርአቱ በሙስና እየተዘፈቀ የሚገኝ በመሆኑ፣ በጋራ መስራታችን ይህንን ታግሎ በማሸነፍ ለማስቀረት ትልቅ አቅም ይሆናል ብለዋል። የስምምነት ሰነዱን መፈራረም ያስፈለገበት ምክንያት በሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃዎች ምክንያት እየተከሰተ ያለውን የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት ጉድለት በማስቀረት በየጊዜው የሚነሱ የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን ለመመለስ እንዲቻል እና በጠንካራ ባለሙያዎች ጠንካራ ተቋማትን መገንባት እንዲቻል መሆኑን የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ኮሚሽነር መሐመድ አብዱላዚዝ ተናግረዋል ሲል የቤ/ጉ/ክ/የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን መረጃውን በማህበራዊ ሚድያ አጋርቷል።

# ኮሚሽኑ ሀገር አቀፍ የፀረ-መስና ኮሚሽኖች ትስስር 7ኛ ጉባኤ አካሄደ

ኮሚሽኑ በወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳይ ላይ ከክልልና ከተማ አስተዳደር የሥነ ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነሮችና ምክትል ኮሚሽነሮች ጋር ውይይት አካሄደ።

በመድረኩ የፌደራል፣ የክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የፀረ ሙስና ኮሚቴዎች ሚና፣ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለ18ኛ ጊዜ እየተከበረ ላለው የፀረ-ሙስና ክብረ በዓል አከባበርና የማጠቃለያ ምዕራፍና ለፀረ-ሙስና ንቅናቄ የሚዲያዎች አጠቃቀም እንዲሁም የሥነ ምግባር ስልጠና ፕሮግራም ላይ ውይይት አካሄዷል።

ሙስና ሀገራዊ ስጋት ስለሆነ የሙስናና ብልሹ አሰራር ጥቆማ ቅበላና የማጣራት ሂደት መረጃና ማስረጃ ማመንጨትንና ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ ውጤት ተኮር በሆነ መልኩ መስራት እንደሚገባ የኮሚሽኑ ኮሚሽነር ዶ/ር ሳሙኤል ኡርቃቶ ገልፀዋል።

በመድረኩ የሀብት ምዝገባና መረጃ የማጣራት ሂደቱ ተመዝግቦ ሰርተፊኬት የያዘና የማጣራት ስራ የተሰራ ተብሎ በመለየት መረጃው ጥራቱን በጠበቀ መልኩ ዘርፍ ተኮር በማድረግ ምዝገባውና ማጣራቱ እንዲደረግ የጋራ አቅጣጫ ተይዟል።

ያለአግባብ በሙስና ወንጀል የተመዘበረ የሀገርና የህዝብ ሀብትና ንብረት በጠቋሚዎች ተጠቁሞ እርግጠኛነቱ ከተረጋገጠ ከተገኘው ሀብት 25 በመቶውን ለጠቋሚው እንደሚሰጥ የሀብት ምዝገባ አዋጁ ይደነግጋል። ሆኖም ሁሉም ኮሚሽኖች በሙስና ወንጀል ፍሬ የተገኘ ሀብት 25 በመቶ ለጠቋሚዎች እንደሚሰጥ የህብረተሰቡን ግንዛቤ በማሳደግ ወደተግባር መግባት እንዳለበት አቅጣጫ በመስጠት 8ኛው ሀገር አቀፍ የፀረ-መስና ኮሚሽኖች ትስስር ጉባኤ በአፋር ክልል ርዕሰ ከተማ ሰመራ በክልሉ የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን አስተባባሪነት የሚካሄድ መሆኑን ተሳታፊች የጋራ አቅጣጫ አስቀምጠዋል።







# ኮሚሽኑ ሙስናን በጋራ ለመከላከል ከሁለት ሚዲያዎች ጋር በጋራ ለመስራት ተስማማ

ፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት እና የፌደራል የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን፣ ሙስናን ለመከላከል በጋራ ለመስራት ስምምነት ተፈራረሙ።

ስምምነቱን የተፈራረሙት የፌደራል የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶ/ር ሳሙኤል ኡርቃቶ እና የፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ አድማሱ ዳምጠው ናቸው።

ተቋማቱ የተፈራረሙት ስምምነት በሀገሪቱ ሙስናን ለመከላከል የሚደረገውን ንቅናቄ በሚዲያ ዘርፍ ለማገዝ ያስችላል ተብሏል።

የፌደራል የስነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶ/ር ሳሙኤል ኡርቃቶ መንግስት በአሁኑ ሰዓት ሙስና የሀገር ብሄራዊ ስጋት መሆኑን ገምግሞ ለመቀነስ ትልቅ ስራ እየሰራ በሚገኝበት ሰዓት ስምምነቱ መፈረሙ ልዩ ያደርገዋል ብለዋል። የተጀመረውን የፀረ-ሙስና ትግል በማጠናከር ፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት የምርመራ ጋዜጠኝነት ስራዎችን እንደሚሰራም ገልጸዋል።

ኮሚሽኑ ከፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት ጋር መፈራረሙ ህዝቡ የተለያዩ ብልሹ አሰራሮችን እንዲጠቁም ያስችለዋልም ነው ያሉት። ሙስናን መታገል የሚቻለው የዜጎችን አመለካከት በመቀየር ሲሆን፣ ትውልድን ለመገንባትም ፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት የተሻሉ ስራዎችን እንደሚሰራም ተናግረዋል።

የፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ አድማሱ ዳምጠው በበኩላቸው፣ ኮሚሽኑ በትክክለኛው ሰዓት ትክክለኛ ሚዲያ እንደመረጠ ተናግረዋል።

በቅርቡ የምርመራ እና የዘጋቢ (ዶክመንተሪ) ጋዜጠኝነት ዳይሬክቶሬት በመክፈት የተለያዩ የምርመራ ስራዎችን እየሰራ እንደሚገኝም አንስተዋል።

ፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት ብልሹ አሰራሮች የሚጋለጡበት፣ በእውነት እና በእውቀት የሚሰራ የሚዲያ ተቋም መሆኑንም ጠቅሰዋል።

በተመሳሳይ ዜና ኮሚሽኑ ሙስናን በጋራ ለመከላከል ከዋልታ ሚዲያና ኮሙኒኬሽን ኮርፖሬት ጋር ዶክመንታሪ ለመስራት የክልልና ከተማ አስተዳደር የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነሮችና ምክትል ኮሚሽነሮች በተገኙበት የመግባቢያ ስምምነት ሰነዱን ተፈራርሟል።

ሀገራዊ የፀረ-ሙስና ብሄራዊ ትግል ንቅናቄ ለመፍጠር ኮሚሽኑ ከዋልታ ሚዲያ ኮሙኒኬሽን ኮርፖሬት ጋር ለህብረተሰቡ አስተማሪና ወቅታዊ መረጃዎችን በዶክመንታሪ ተደራሽ ለማድረግ ስምምነቱ እንደተደረገ የኮሚሽኑ ኮሚሽነር ዶ/ር ሳሙኤል ኡርቃቶ አመላክተዋል።

ኮሚሽነር ዶ/ር ሳሙኤል አክለውም ከሙስና የፀዳ ትውልድ ለመፍጠር፣ ለሙስና የተጋለጡ ተቋማት በግልፅነት እንዲሰሩ ለማድረግ፣ በመረጃና ማስረጃ የተመረኮዘ ብልሹ አሰራሮችን ለማጋለጥና ለመጠቆም የሚዲያዎች ሚና ላቅ ያለ በመሆኑ በዶክመንታሪ የተዘጋጀ ሰነድ በማዘጋጀት ለህብረተሰቡ ማድረስ እንደሚገባ ገልፀው፣ የክልልና የከተማ አስተዳደር የሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች ከዋልታ ሚዲያም ሆነ ከሌሎች ጋር በጋራ ለመስራት ስምምነት ከተፈራረሙባቸው ሚዲያዎች ጋር ለፀረ-ሙስና ንቅናቄው በጋራ መስራት እንደሚችሉ ጠቁመዋል።

ዋልታ ሚዲያና ኮሙኒኬሽን ኮርፖሬት ሀገርን በመገንባት በቅርበት ከሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ተደራሽ የሆነ ዶክመንታሪ የሚሰራ መሆኑን የዋልታ ሚዲያ ኮሙኒኬሽን ኮርፖሬት ዋና ስራ አስፈፃሚ ዶ/ር ንጉሴ መሸሻ ጠቁመው፣ ስምምነቱ ዶክመንታሪ ለመስራት የተደረገ ቢሆንም የምርመራ ዘገባንም ያለስምምነት ከኮሚሽኑ ጋር በጋራ ሙስናን ለመከላከል እንደሚሰራ ተናግረዋል።







ኮሚሽኑ ከዋልታ ሚዲያና ኮሙኒኬሽን ኮርፖሬት ጋር ያደረገው ስምምነት የዶክመንተሪና ሳምንታዊ የጥያቄና መልስ ውድድርን ያካተተ ሲሆን እስከ ሰኔ/2015 ዓ.ም ድረስ እንደሚዘልቅ ተጠቁሟል።

ኮሚሽኑ ከኢትዮጵያ ብሮድካስት ኮርፖሬት ጋርም በጋራ የተለያዩ ስራዎችን ለመስራት መፈራረማቸው ይታወሳል።

# በለሚ ኩራ ክ/ከተማ በመሬት ዝርፊያ ከተጠረጠሩ 37 ግለሰቦች ውስጥ 12ቱ በቁጥጥር ስር ዋሉ

በመሬት ላይ ሲደረግ በቆየ የማጣራት ስራ በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ከ37 ተጠርጣሪዎች ውስጥ 12 ግለሰቦች በቁጥጥር ስር መዋላቸውን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስታወቀ።

ከተማ አስተዳደሩ ከመሬት ዝርፍያ ጋር በተያያዘ ሲያደርገው በቆየው የማጣራት ስራ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ የወረዳ ዋና ስራ አስፈፃሚን ጨምሮ የክ/ከተማ በመሬት ጉዳይ ይወስኑ የነበሩ አመራሮች እና ባለሙያዎች በቁጥጥር ስር መዋላቸው ተገልጿል።

በተጨማሪም ደላሎችና ከህብረተሰቡ ውስጥ በዚህ ድርጊት የተሳተፉትን ጨምሮ 37 ሰዎችን በመለየት ለህግ እንዲቀርቡ እንቅስቃሴ ከተጀመረ ጊዜ አንስቶ እስካሁን ድረስ 12 ግለሰቦች በፖሊስ ቁጥጥር ስር መዋላቸው ተመላክቷል።

በቁጥጥር ስር የዋሉት ግለሰቦች፡-

1. ለምለም አባይነህ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ ወረዳ 4 ዋና ስራ አስፈፃሚ፣
2. አቶ ከፍያለው አሰፋ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ የፕሮሰስ ካውንስል አመራር የነበሩ (በመሬት ጉዳይ ውሳኔ የሚሰጡ የነበሩ)፣
3. አቶ ዋሲሁን ሰውነት የለሚ ኩራ ክ/ከተማ የፕሮሰስ ካውንስል አመራር የነበሩ (በመሬት ጉዳይ ውሳኔ የሚሰጡ የነበሩ)፣
4. አቶ ኢብራሂም ሀሰን የለሚ ኩራ ክ/ከተማ የፕሮሰስ ካውንስል አመራር የነበሩ (በመሬት ጉዳይ ውሳኔ የሚሰጡ የነበሩ)፣
5. አቶ ሃይለየሱስ ደስታ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ የፕሮሰስ ካውንስል አመራር የነበሩ (በመሬት ጉዳይ ውሳኔ የሚሰጡ የነበሩ)፣
6. አቶ ዳዊት ከልሌ የቴክኒካል ካርታ ዝግጅት ባለሙያ፣
7. አቶ ልኡልሰገድ ታደሰ የቴክኒካል ካርታ ዝግጅት ባለሙያ፣

ከመንግስት ተቋማት ውጪ በጉዳዩ ተሳታፊነት በቁጥጥር ስር የዋሉ ግለሰቦች

8. አቶ አየለ ጉቱ፣
9. አቶ ጎሳዬ ደሜ፣
10. አቶ በፍቃዱ ወንደሰን፣
11. አቶ ሮባ ደበሌና
12. አቶ መታሰቢያ አባተ ናቸው።

በሌላ መረጃ መንግስት ለጀመረው የፀረ-ሙስና ትግል ስኬታማነት የህብረተሰቡ ተሳትፎ ተጠናክሮ እንዲቀጥል የአዲስ አበባ ፖሊስ ጥሪ ያስተላለፈ ሲሆን፣ በሙስና ወንጀል የተጠረጠሩ ግለሰቦች ላይ ምርመራውን አጠናክሮ መቀጠሉንም አስታውቋል።

የአዲስ አበባ ፖሊስ በማኅበራዊ ትስስር ገፁ ባወጣው መረጃ መሰረት፡-

1ኛ. ሀቢባ ኡመር የለሚ ኩራ ክ/ከተማ የመሬት ልማት አስተዳደር ፅ/ቤት ሀላፊ፣

2ኛ. ተስፋዬ ግርማ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ የመሬት ልማት አስተዳደር ፅ/ቤት ምክትል ሀላፊ፣

3ኛ. በቃሉ ፀደቀ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ የመሬት አስተዳደር ባለሙያ፣

4ኛ. ጭምዴሳ ፋለአ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ የመሬት ልማት አስተዳደር ባለሙያ እንዲሁም

5ኛ. ልኡል ተረፈ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ የወረዳ 4 አስተዳደር ዋና ስራ አስፈፃሚ ሆነው እየሰሩ በነበረበት ወቅት ስልጣናቸውን ያለአግባብ በመጠቀም ሀሰተኛ ሰነድ አዘጋጅተው የመንግስት እና የህዝብ መሬት እንዲመዘበር በማድረጋቸው በተጠረጠሩበት ወንጀል በህግ ይፈለጋሉ።

እነዚህ ግለሰቦች ያሉበትን የሚያውቅ ወይም መረጃ ያለው ማንኛውም ግለሰብ በአቅራቢያው በሚገኝ ፖሊስ ጣቢያ ወይም በአዲስ አበባ ፖሊስ በግንባር በመቅረብ ወይም በስልክ ቁጥር 991፣ 0111110111 እና 0111568311 መረጃ በመስጠት የዜግነት ድርሻውን እንዲወጣ የአዲስ አበባ ፖሊስ ጥሪ አስተላልፏል ሲል አዲስ ሚዲያ ኔትወርክ በማህበራዊ ድረ-ገፁ መረጃውን አጋርቷል።







# የ2015 ዓ.ም አለም አቀፍ የፀረ-ሙስና ቀን "ሙስናን መታገል በተግባር!" በሚል መሪ ቃል ህዳር 30 በደማቅ ሁኔታ ይከበራል

ኮሚሽኑ በአለም አቀፍ ደረጃ ለ19ኛ በሀገራችን ለ18ኛ ጊዜ "ሙስናን መታገል በተግባር" በሚል መሪ ቃል የሚከበረው አለም አቀፍ የፀረ-ሙስና ቀን አከባበር ለየት ባለ መልኩ ህዳር 30 በደመቀ ሁኔታ በአዲስ አበባ ከተማ በዓሉን ለማክበር የማስፈፀሚያ ዕቅድ በማዘጋጀት ከክልልና ከተማ አስተዳደር የሥነ ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች ጋር ውይይት ያካሄደ ሲሆን፣ የሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ባለድርሻ አካላት ማስተባበሪያ ስራ አስፈፃሚ አቶ አዲስ ለማ የማስፈፀሚያ ዕቅዱን ሲያቀርቡ በዓሉ በፌደራልም ሆነ በክልል በሁሉም የህብረተሰብ ደረጃ ለማክበር እንዲረዳ የተለያዩ ሁነቱን የሚያሳልጡ አብይና ንዑሳን ኮሚቴዎችን በማዋቀር በተለያዩ ዝግጅቶች እንደሚከበር ለመድረኩ ተሳታፊዎች ገልፀዋል።

በሀገር አቀፍ ደረጃ ቀኑ ሲከበር ሙስናን ለመከላከል እየተደረገ ያለውን አለማቀፋዊ ብሎም ሀገራዊ ጥረት ህብረተሰቡ እንዲገነዘብና በፀረ-ሙስና ትግሉ ሀገራዊ ንቅናቄ ለመፍጠርና ተሳታፊ እንዲሆን በማሰብ በዓሉ በተለያዩ ዝግጅቶች እንዲከበር ለክልልና ከተማ አስተዳደር የሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች የማስፈፀሚያ ዕቅዱን እንደየክልልና ተቋማት ነባራዊ ሁኔታ አውርዶ መተግበር እንደሚገባ የኮሚሽኑ ም/ኮሚሽነር አቶ ወዶ አጦ አመላክተው፣ በዓሉ ሲከበር ፌደራልን ጨምሮ ሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደር የሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች የፀረ-ሙስና ትግሉን ለማሳለጥ የሚዲያ አካላትን በስፋት በመጠቀም በተለያዩ ዝግጅቶች እንዲከበር አቅጣጫ አስቀምጠው ከፍተኛ የመንግስት አመራሮች፣ የክልሎችና ከተማ አስተዳደር የሥነ ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽነሮች እንዲሁም ባለድርሻ አካላት ሌሎች ተጋባዥ እንግዶች በተገኙበት ህዳር 30/2015 ዓ.ም የበዓሉ ማጠቃለያ እንደሚካሄድ ጠቁመዋል።

በሌላ መረጃ የበዓሉን አከባበር አስመልክቶ በኮሚሽኑ አዳራሽ ለተለያዩ ሚዲያዎች መግለጫ የሰጡት የኮሚሽኑ ምክትል ኮሚሽነር አቶ ወዶ አጦ ሙስና ልማትን በሚያዳከም የሀገርን ዕድገት የሚያቀጭጭ፣ የሞራልና የሥነ ምግባር ቀውስ እንዲባባስ፣ ሰላምና መረጋጋት እንዳይኖር፣ ህዝብ በመንግስትና በህግ የበላይነት ላይ አመኔታ እንዲያጣ የሚያደርግ አደገኛና ድንበር ዘለል ባህሪ ያለው አለማቀፋዊ ወንጀል መሆኑን ጠቅሰዋል።

የፌደራል የሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ባደረገው ጥናትም ሙስና በሀገሪቱ ካለው የኑሮ ውድነትና ከስራ አጥነት ቀጥሎ የሀገር ችግር መሆኑን መረጋገጡን አመላክተዋል።

የተባበሩት መንግስታት የፀረ-ሙስና ድንጋጌ ፀድቆ ለፊርማ የቀረበበት በፈረንጆቹ ታህሳስ 9/2003 ወይም በኢትዮጵያ አቆጣጠር ሕዳር 30 ቀን ዓለም አቀፍ የፀረ-ሙስና ቀን ተከብሮ ይውላል ያሉ ሲሆን፣ ኢትዮጵያም የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ አንድ አካልና የድንጋጌው ፈራሚና አፅዳቂ ሀገር እንደመሆኗ ቀኑን ለ18ኛ ጊዜ ታከብራለች ብለዋል።

የሙስና ድርጊቶች ሲፈጸሙ የሚመለከት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በ9555 ነጻ የስልክ መስመርና በሌሎች የጥቆማ አማራጮች ተጠቅሞ ጥቆማ በመስጠት የሚጠበቅበትን ሃላፊነት እንዲወጣ ጥሪ አቅርበዋል። ከሚዲያዎች ለቀረቡ ጥያቄዎች የተቋሙን ኃላፊነትና ተግባር አስመልክተው ማብራሪያ የሰጡ ሲሆን የበዓሉን አከባበር አስመልክቶ በሀገር አቀፍ ደረጃ በሁሉም ክልሎች እስከ ታች መዋቅር እንደየክልላቸው ተጨባጭ ሁኔታ በያዙት ዕቅድ መሰረት እየተከበረ መሆኑን ገልፀው በፌደራል ደረጃ ከሁሉም ባለድርሻ አካላት፣ ከሲቪክ ማህበራት፣ ከሃይማኖት ተቋማትና ሌሎች አካላት በተገኙበት ህዳር 30/2015 ዓ.ም የበዓሉ ማጠቃለያ በዓል እንደሚከበር ተጠቁሟል።








አለም አቀፍ የፀረ-ሙስና ቀን በዓል ሙስናና ብልሹ አሰራር የሚያስከትላቸውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳት በተመለከተ የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ዝግጅቶችን በማካሄድ ህብረተሰቡ የፀረ-ሙስና ትግል አጋር እንዲሆን ለማነቃቃት ታስቦ ይከበራል።

በዓሉ በሀገር አቀፍ ደረጃ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና በክልል የስነምግባር የፀረ-ሙስና ኮሚሽን እንዲሁም በተለያዩ የመንግስት ተቋማት እና የልማት ድርጅቶች በደማቅ ሁኔታ እየተከበረ መሆኑን በተለያዩ የማህበራዊ መገናኛ ምንጮች መረጃውን መመልከት ችለናል።

# ቆይታ



የፌደራል፣ የክልልና የከተማ አስተዳደሮች የፀረ-ሙስና ተቋማት በህግ የተሰጣቸውን ሙስናን የመከላከል ተልዕኮ በአግባቡ ለመወጣት የትውልድን የሥነምግባር እና የሞራል እሴቶች መገንባት፣ በመንግስት ተቋማትና በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የሚስተዋሉ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች እንዲለዩና እንዲፈቱ ማድረግ፣ ሀብት መመዝገብና ትክክለኛነቱን በማረጋገጥ በተቋማት የግልፀኝነትና የተጠያቂነት ስርዓት እንዲሰፍን ማድረግና የተለያዩ ባለድርሻ አካላትንና መላውን ህበረተሰብ የፀረ-ሙስና ትግሉ ባለቤት እንዲሆን ማስቻል ሲሆን፣ የአማራ ክልል የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ይህን ዓለማ አንግቦ ስራዎችን እያከናወነ ይገኛል።

የ‹‹ፀረ-ሙስና›› ጋዜጣ የአምስተኛ ዕትም እንግዳችን የአማራ ክልል የስነምግባር የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር አቶ ሀብታሙ ሞገስ ናቸው። የ‹‹ፀረ-ሙስና›› ጋዜጣ ከኮምሽነር ሀብታሙ ሞገስ ጋር ያደረገችውን ቆይታ ይዛ ቀርባለች። መልካም ንባብ...

## «ሙስና በአንድ ተቋም ብቻ ሊወገድ ስለማይችል ህዝቡ መረጃና ማስረጃን መሠረት በማድረግ ጥቆማ በመስጠት ሊታገል ይገባል»

**- የአማራ ክልል የስነምግባር የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር አቶ ሀብታሙ ሞገስ**

**የ‹‹ፀረ-ሙስና›› ጋዜጣ፡-** ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን ከመከላከል አኳያ በአማራ ክልል የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን እየተከናወኑ ያሉ ስራዎች እንዲሁም ሀገራዊ የፀረ-ሙስና ኮሚቴ ከተቋቋመ በኃላ ሙስናን ለመታገል ያላችሁ እቅስቃሴ ምን ይመስላል?

**ኮሚሽነር ሀብታሙ ሞገስ፡-** እንደኛ ክልል ከበፊትም በክልላችን ሙስናና ብልሹ አሰራረን ከመከላከል አኳይ ሰፊ ተግባራት እየተከናወኑ ይገኛል፤ ሀገራዊ የፀረ-ሙስና ኮሚቴ ከተቋቋመ በኃላም ስራውን የበለጠ በማጠናከር የፀረ-ሙስና ትግሉ በአንድ ተቋም ተጀምሮ የሚጠናቀቅ ባለመሆኑ ከእኛ ተቋም ጋር ሊሰሩ የሚችሉ አጋር አካላት ጋር በመነጋገር ማለትም ከፖሊስና ከአቃቢ ህግ ጋር በጋራ በመሆን እስከታች ድረስ ያሉ አካላትን መድረክ በመፍጠር በወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳይ እንዴት ሙስናን በጋራ በቅንጅት እንከላከል የሚለውን የጋራ የማድረግ ስራ ተሰርቶ የስምምነት ሰነድ በማዘጋጀት ቅንጅታዊ አሰራርን በሚያጠናክር መልኩ ወደ ስራ ገብተናል። በሌላ መልኩ በምክር ቤት ደረጃ እስከታች ድረስ ህብረተሰቡን ተደራሽ የሚያደርጉ ከመሆናቸውና የህዝብ ውክልና ይዘው የመጡ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ የምክር ቤት አባላትን በሙስና ትግሉ ዙሪያ ሚናቸው ምን መሆን እንዳለበት በአፈጉባኤ የተመራ መድረክ በመፍጠር የጋራ ውይይት ማድረግ ተችሏል።

**የ‹‹ፀረ-ሙስና›› ጋዜጣ፡-** በክልሉ ያሉ የመንግስት ተሿሚ፣ ሰራተኛ እንዲሁም የህዝብ ተመራጭ ሀብት ከመመዝገብና የተመዘገቡትን ከማጣራት አንፃር የተከናወኑ ስራዎች ካሉ ቢያብራሩልን?

**ኮሚሽነር ሀብታሙ ሞገስ፡-** ከሃብት ምዝገባ ጋር በተያያዘ እስካሁን ድረስ በአዋጁ መሰረት ሀብታቸውን ማስመዝገብ ያለባቸው የመንግስት ተሿሚና ሰራተኞች እንዲሁም የህዝብ ተመራጮች ሀብታቸውን የመመዝገብ ስራ እየተሰራ ነው፤ በሚፈለገው ልክ ተሰርቷል ብለን አንወስድም፣ ምክኒያቱም ሀብታቸውን ያላስመዘገቡ ብዙ ተሿሚዎች፣ ሰራተኞችና የህዝብ ተመራጮች አሉ፤ ስለሆነም በአሁኑ ሰዓት ሰፊ እንቅስቃሴ እያደረግን ሲሆን ሀብት መመዝገብ ብቻውን በቂ ስላልሆነ የተመዘገበው ሀብት ምን ያህል ከገቢው ጋር የተመጣጠነ እና በህጋዊ መልኩ የተገኘ ነው የሚለውን የማጣራት ስራ እየሰራን እንገኛለን።

ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ ወደ 60 የሚጠጉ ከገቢያቸው መጠን በላይ ሀብት የተገኘባቸውና በተገቢው ሀብታቸውን ያላስመዘገቡ እንዲሁም የሌላቸውን ሀብት ጭምር አስመዝግበው የተገኙ ሀብት አስመዝጋቢዎች ምርመራ እንዲጣራ ወደ ፖሊስ መላክ ተችሏል።

**የ‹‹ፀረ-ሙስና›› ጋዜጣ፡-** የሙስና ወንጀል መረጃዎችን ወደ ፖሊስ ከተላከ በኃላ ክትትላቹህ በምን ደረጃ ይገኛል?

**ኮሚሽነር ሀብታሙ ሞገስ፡-** ወደ ፖሊስ ከመላካችን በፊት ከፖሊስ ጋር በምን አግባብ መሰራት አለብን በሚል ተወያይተናል፤ የተወያየንበት ምክኒያት ህብረተሰቡ ብዙ ጊዜ ሀብት ትመዘግባላችሁ እንጂ ከዚያ በላይ ምን ሰራችሁ፣ ሀብት መመዝገብ ብቻ ምን ውጤት ያመጣል የሚል እውነትነት ያለው ሰፊ ጥያቄዎች ስለሚያነሳ፣ ያነን መነሻ በማድረግ የማጣራቱን ስራ ስንሰራ፣ ፖሊስ ደግሞ የኛን የማጣራት ስራ ተቀብሎ የራሱን ሙያዊ አስተያየት ጨምሮ ወደ ክስና ወደ



ፍርድ አደባባይ መቅረብ ያለባቸው ወደ አቃቢ ህግና ወደ ፍርድ ቤት መላክ ስላለበት ከእነሱ ጋር ተነጋግረን ከእኛ የተላኩትን የሀብት ማጣራት ስራዎች አሁን ፖሊስ ይዞ በሁለት አቅጣጫ ከፋፍሎ ሁለት የምርመራ ቡድን ተቋቁሞ በአሁኑ ሰዓት እስከ ታች ድረስ ወርዶ የማጣራትና የክትትል ስራው እየተከናወነ ይገኛል።

**የ‹‹ፀረ-ሙስና›› ጋዜጣ፡-** ኮሚሽኑ ከፍትህ አካላት፣ ከፖሊስና ከሚዲያ እንዲሁም ከሌሎች አጋር ተቋማት ጋር ሙስናና ብልሹ አሰራርን ከመከላከልና ስነምግባርን ከመገባት አኳያ በቅንጅት እየተከናወኑ ያሉ ስራዎች ካሉ ቢገልፁልን?

**ኮሚሽነር ሀብታሙ ሞገስ፡-** ቅንጅታዊ አሰራራችን መግቢያችን ላይ እንደነገርኩህ ሙስና በባህሪው በአንድ ተቋም ተጀምሮ በአንድ ተቋም የሚጠናቀቅ አይደለም፣ ስነምግባር ግንባታው በተመሳሳይ እኛ አጋር አካላት ብለን የለየናቸው አሉ፤ ለምሳሌ- ከስነምግባር ግንባታ ጋር በተያያዘ ከትምህርት ቤቶች ጋር የሚሰራ ስራ በመኖሩ ከትምህርት ቢሮ አመራሮችና ከሚመለከታቸው ባለሙያዎች ጋር መድረክ በመፍጠር እንዴት አድርገን ትምህርት ቤቶች ላይ የስነምግባር መገንባት ስራ እንስራ በሚል በተቻለ መጠን በትምህርት ቤት የስነምግባር ክበባት ተጠናክረው እንዲቋቋሙና በጥብቅ ክትትል ድጋፍ እየተደረገላቸው ስነ ምግባር ላይ አተኩረው እንዲሰሩ የመግባባት ስራ የተሰራበት ሁኔታ ሲኖር፤ በሌላ በኩል ከፍትህ አካላት ጋር ደግሞ ፖሊስና ከአቃቢ ህግ እስከ ታች ድረስ ያሉት የሙስና ወንጀል መርማሪ ፖሊስና የፍትህ ቢሮ ኃላፊዎች በተገኙበት እንዴት ቅንጅታዊ አሰራራችን አጠናክረን የፀረ-ሙስና ትግሉን እንምራው በሚል ተነጋግረን የስምምነት ሰነድም የተፈራረምንበት ሁኔታ ነው ያለው።

በተጨማሪም ምክር ቤቶችን አጋር አደርገን የሄድንበት ርቀት ራሱን ችለን የፀረ-ሙስና ትግሉን ለማሳለጥ የምክር ቤቶች ሚና ምን ይመስላል የሚለውን የምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴዎችና ሌሎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የጋራ መድረክ ፈጥረን የተነጋገርንበትና የትግሉ አንድ አካል እንዲሆኑ የተደረጉበት ሁኔታ ሲኖር፣ ከሚዲያ አካላትም ጋር በተያያዘ በልዩ ሁኔታ የራሱን መድረክ ፈጥረን ተደጋግፍን እንድንሰራ የማድረግ ስራ ሰርተናል። አሁን ባለው ሁኔታ ሚዲያዎች የኛን ተቋም ለማገዝ የሚያደርጉት ጥረት የሚበረታታ ነው።

**የ‹‹ፀረ-ሙስና›› ጋዜጣ፡-** የፌድራል የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ስራዎች ለማከናወን ይረዳው ዘንድ ተቋማትን በዘርፍ ከፋፍሎ እያከናወነ ይገኛል። ከተከናወኑ ተግባርት መካከል በፍርድ ቤት ዘርፍ፣በትምህርት ዘርፍ፣ በጉሙሩክና ገቢዎች እንዲሁም በንግድ ዘርፍ ጥናቶችን በማካሄድ ከዘርፉ ባለቤትና ከአጋር አካላት ጋር ውይይት ማካሄድ ችሏል። ከዚህ አኳያ በአማራ ክልል የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የተከናወነ ተግባር ካለ እና በቀጣይ ልትሰሩት ያሰባችሁት ስራ ካለም ቢያብራሩልን?

**ኮሚሽነር ሀብታሙ ሞገስ፡-** ከተቋማት አሰራር ስርዓት ጥናት ጋር በተያያዘ እንደኛ ክልል ጥናት ያደረግንባቸው የተለያዩ ዘርፎች አሉ፤ እንደ ፌደራል ከተግባባንባቸው ውስጥ በአሁኑ ሰዓት ከንግድ ዘርፍ ጋር በተያያዘ የስሚንቶ አጠቃላይ ክፍፍልንና የንግድ ስርዓቱን በተመለከተ ጥናት በማካሄድ ብልሹ አሰራሮች ያሉበት መሆኑን ስላመንበት እንዲስተካከል ለንግድ ቢሮ ያሳወቅን ሲሆን፣ የምርት ስርጭቱ እየተከፋፈለበት ያለው አግባብ ትክክል አለመሆኑን ማሳወቅ ችለናል። ለፖሊስ ብልሽት በፈጠሩ አካላት ላይ እርምጃ እንዲወስድ የማሳወቅ ስራ ተሰርቷል።

በተጨማሪም ከገቢዎች ጋር በተያያዘ ያለው የአሰራር ሁኔታ ምን ይመስላል የሚለውን ጥናት አካሄደን በማጠናቀቅ የሚስተካከሉ ነገሮች እንዲስተካከሉ ለገቢዎች ቢሮ መላክ ችለናል።

ከመሬት ጋር በተያያዘ ደግሞ በልዩ ሁኔታ የመንግስት ቤቶች አስተዳደር የቀበሌ ቤቶች በምን አግባብ እየተዳደሩ ነው የሚለውን የማጥናት ስራ ሰርተን የሚመለከታቸው የከተማ ከቲባዎችና የከተማና መሰረተ ልማት መምሪያ ኃላፊዎችና የቢሮ ኃላፊዎች በተገኙበት በጋራ ውይይት አድርገን መግባባት ፈጥረናል። ከሲቪል ሰርቪስ የሰው ኃይል ስምሪቱና ሌሎች የልማት ድረጅቶች አጠቃላይ የሰው ኃይልና የፋይናንስ ስርዓታቸው ምን ይመስላል የሚለውን እየተጠና ያለበት ሁኔታ ስላለ፣ ጥናቱ ሲያልቅም ለህዝብ ይፋ የሚደረግ ይሆናል።

**የ‹‹ፀረ-ሙስና›› ጋዜጣ፡-** እንደ ክልሉ ኮሚሽን ተግባራትን ስታከናውኑ የሚያጋጥሟችሁ ተግዳሮቶች ምንድን ናቸው?

**ኮሚሽነር ሀብታሙ ሞገስ፡-** በዋናነት ተግባራትን ስናከናውን የሚያጋጥሙን ችግሮች በመሰረታዊነት የህግ ማዕቀፋችን አልተሻሻለም፣ ከምክር ቤት ጋር በመነጋገራችን በቅርቡ ይሻሻላል ብለን እናስባለን። ከአደረጃጀትና ከአሰራር ጋር ተያይዞ ያለው አደረጃጀት በሚፈለገው ልክ የተሟላ ባለመሆኑ ብዙ የተጓደሉ የወረዳና የተቋም ቦታዎች ሊሟሉ የሚገባ ሲሆን፣ አንዳንድ ተቋማት ለጉዳዩ የተለዬ ትኩረት ሰጠው በመደገፍ በኩል ውስንነቶች እንዳሉ አይተናል፤ በአሁኑ ወቅት በመንግስት በኩል ያለው ቁርጠኝነት ሁኔታ የተሻለ ስለሆነ ህብረተሰቡን አጋር አድርገን ለመንቀሳቀስ እየሄድንበት ያለው ጥረት እንደጥሩ በመወሰዱ ችግሩን እንፈታዋልን ብለን እናስባለን።

**የ‹‹ፀረ-ሙስና›› ጋዜጣ፡-** ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን ከመከላከል አኳያ ከመንግስት፣ ከፍትህ አካላት፣ ከሃይማኖት ተቋማትና ከህዝቡ እንዲሁም ከሚመለከታቸው አካላት ምን ይጠበቃል?

**ኮሚሽነር ሀብታሙ ሞገስ፡-** ሙስናን ከመከላከል አኳያ በመሰረታዊነት እንደመንግስትና ድረጅት በአሁኑ ሰዓት በተለዬ ቁርጠኝነት ወይም ትኩረት ሰጥቶ ሙስና የስርዓቱ ችግር እልፍም ሲል ይህንን የመልካም አስተዳደር ችግር ህብረተሰቡ በሰፊው እያማረረው ስለሆነ እንፍታው በሚል በቁርጠኝነት ወደ ተግባር ተገብቷል። ራሱን የቻለ የፀረ-ሙስና ኮሚቴ ተቋቁሞ እየሄደበት ያለ ስለሆነ ያለው እንቅስቃሴ በጥሩ በኩል ስለምናየው እስከመጨረሻው መቀጠል አስፈላጊ ነው። የኃይማኖት ተቋማትና ሌሎች መሰል አካላት ከምንም በላይ የስነምግባር ግባታውና የሙስና ትግሉ ላይ የሃይማኖት ተቋማት አይተኬ ሚና አላቸው። ስለዚህ የአይማኖቱን ቀኑና በማስተማር ህብረተሰቡ በላቡ፣ በወዙ ሰርቶ እንዲያድር፤ የማይገባውን እንዳይወስድ፤ በማስተማር በኩል ሰፊ ስራ መሰራት እያለበት እየተሄደበት ያለው ርቀት ደካማ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ሙስና በዚህ ልክ እየተስፋፋ ይገኛል።

ህብረተሰቡ አሁን እንደጀማመረው ሙብቴን በገንዘብ አልገዛም ብሎ ሌብነትን ማውገዝ፣ ሙሰኞችን ማጋለጥና መጠቆም ከህብረተሰቡ ይጠበቃል፤ ከዚያ በኋላ ወደ ፍርድ አደባባይ ሲቀርቡ በቂ የምስክርነት ቃል በመስጠት ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድባቸው የማድረጉ ስራ እንዳለ ሁኖ፣ ከመከላከል ዙሪያ ግን ህብረተሰቡ በባለቤትነት ሁኖ ሙብቴን በገንዘብ አልገዛም የሚል ሞጋች ህብረተሰብ ሊፈጠር ይገባል የሚል ሀሳብ አለኝ።

**የ‹‹ፀረ-ሙስና›› ጋዜጣ፡-** በ2015 ዓ.ም «ሙስናን መታገል በተግባር» በሚል መሪ ቃል በአለም አቀፍ ደረጃ ለ19ኛ ጊዜ በሀገራችን ደግሞ 18ኛ ጊዜ የፀረ-ሙስና ቀን ይከበራል። የአማራ ክልል የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በምን መልኩ ለማክበር ተዘጋጅቷል?

**ኮሚሽነር ሀብታሙ ሞገስ፡-** አለም አቀፍ የፀረ-ሙስና ቀንን በተመለከተ እንደ ክልላችን ሰፊ ዝግጅት አድርገናል፤ ከዝግጅቱ ውስጥ በፌደራል ደረጃ የተዘጋዘጀውን እቅድ ወደራሳችን ክልል በመውሰድ እቅዱን በማሻሻል፣ የሚጨመረውን በመጨመርና የሚቀነሰውን በመቀነስ የሚመለከታቸውን አካላት በመጋበዝ ኦረቴሽን በመስጠት፣ እራሱን የቻለ እቅድ አዘጋጅተን በምን አግባብ እንምራው የሚለውን እስከታች ህብረተሰቡ ድረስ በየደረጃው ያለ የመንግስት ከፍተኛ አመራር አስተዳዳሪና ከቲባዎች እንዲመሩት የማድረግ ስራ፣ እንዲሁም በቢሮ ደረጃ የቢሮ ኃላፊወች እንዲመሩት የማድረግ ስራ እየተሰራ ይገኛል። በትምህርት ቤቶች ላይ የጥያቄና መልስ ውድድር፣ ስፖርታዊ ውድድርና ሌሎችም በማሳተፍ በተቻለ መጠን ህብረተሰቡን ወደ ንቅናቄ ማስገባት ስራ እየተሰራ ሲሆን፤ በክልል ደረጃ የማጠቃለያ ፕሮግራም በባህርዳር ከተማ ይኖረናል። በእለቱ የተለያዬ የህብረተሰብ ክፍል ጠርተን በተሻለ እንቅስቃሴ ግንዛቤ የሚፈጠርበት ሂደት ይኖራል።

በአጠቃላይ በየደረጃው ያለ አመራር ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት በእየተቋሙና በሚመራው አካባቢ የተለዬ ርብርብ ማድረግ እና ምንድን ነው ከእኔ ተቋም አኳያ ያሉ የሙስናና የስነምግባር ግድፈቶች የሚለውን ለይቶ ነቅሶ በማውጣት መታገል ይኖርበታል፤ ባለሙያዎችም በዛው ልክ መታገል ይኖርባቸዋል።

የማያሰሩ አሰራሮች፣ ህጎችና መመሪያዎች ካሉ ማሻሻል፣ ህብረተሰቡ ደግሞ አይንና ጆሮውን ለፀረ-ሙስና ትግሉ በመስጠት ሰፊ ርብርብ በማድረግ አሁን ያለውን የሌብነት ተግባር ከጎናችን በመሆን ሊታገል ይገባል የሚል መልክት ማስተላለፍ እፈልጋለሁ።

# ሳይቃጠል በቅጠል

የፌደራል፣ የክልልና የከተማ አስተዳደር የስነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች ሥነምግባርን የመገንባት፣ ሙስናን የመከላከልና የፀረ-ሙስና ትግሉን በበላይነት የማስተባበር ሀላፊነት በህግ የተሰጣቸው አካላት ናቸው። የፀረ-ሙስና ተቋማት በህግ የተሰጣቸውን ሙስናን የመከላከል ተልዕኮ በአግባቡ ለመወጣት የትውልድን የሥነምግባር እና የሞራል እሴቶች መገንባት፣ በመንግስት ተቋማትና በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የሚስተዋሉ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች እንዲለዩና እንዲፈቱ ማድረግ፣ ሀብት መመዝገብና ትክክለኛነቱን በማረጋገጥ በተቋማት የግልፀኝነትና የተጠያቂነት ስርዓት እንዲሰፍን ማድረግና የተለያዩ ባለድርሻ አካላትንና መላውን ህበረተሰብ የፀረ-ሙስና ትግሉ ባለቤት እንዲሆን ማስቻል ነው።

ኮሚሽኑ ከሚያከናወናቸው ተግባራት መካከል ከሚመጡለት መረጃወች በመነሳት በመንግስት ተቋማትና የልማት ድረጅቶች እንዲሁም ህዝባዊ ድረጅቶች አስቸኳይ የሙስና መከላከል ጥናት በማድረግ በተገኘው ግኝት መሰረት ምክረ ሀሳብ ይሰጣል።

በመሆኑም በኢፌዲሪ ጤና ሚኒስቴር ኤካ ኮተቤ አጠቃላይ ሆስፒታል መስከረም 26/2014 ዓ.ም ባወጣዉ የህክምና መሳሪያዎች ግልጽ የግዢ ጨረታ አሸናፊዉ ድርጅት ሐመርናሳ ፋርማሲዩቲካልስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር በስፔሲፊኬሽን መሰረት አልትራ ሳውንድ እና የአልትራሳዉንድ አጋዥ እቃዎች እንዲሁም የማሽኑን ተከላና ስልጠና ለማቅረብ ጨረታ አሸንፎ ውል የወሰደ ቢሆንም በገባው ውል መሰረት እቃዎቹን አሟልቶ አላስገባም በሚል ጥቅምት 21/2015 ዓ.ም ለኮሚሽኑ በቀረበ የጥቆማ መነሻነት መሰረት የአስቸኳይ የሙስና እና ብልሹ አሰራሮች መከላከል የማጣራት ስራ አካሄዷል።

አስቸኳይ የማጣራት ስራው የተከናወነው ኤካ ኮተቤ አጠቃላይ ሆስፒታል በአካል በመገኘት ለማጣራት ስራው የሚያስፈልጉ ሰነዶችና ማስረጃዎችን በማሰባሰብና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይት በማድረግ ሲሆን፣ በጥናቱ በግዢ ጨረታ ሰነድ መዘርዝር (specification) መሰረት የታዘዙ ፕሮቮች ለ2 አልትራሳዉንድ 10 ፕሮቮች ሲሆኑ የጨረታ አሸናፊው ድርጅት ገቢ ያደረጋቸዉ 6 ፕሮቮች ብቻ መሆናቸው፣ አሸናፊው ድርጅት Curved (convex) probe×2፣ Linear probe×2፣ Phased array prob×2 ገቢ ቢያደርግም ለ2 አልትራሳዉንድ 4 ፕሮቮች ማለትም Micro curved probe ×2 እና Endo cavity probe×2 ለሆስፒታሉ ገቢ አለመደረጋቸዉን፣ የአልትራሳዉንዱ ማሽን አጋዥ ቁሳቁሶች ማለትም ultrasound paper 100 roll ×2, gel 250 ml ×4, ከ200 ጥቅል (roll) ዉስጥ 2 ጥቅል ብቻ ገቢ የተደረገ መሆኑና አንድ ሊትር ጄል ገቢ አለመደረጉን ከሰነድ፣ከኮሚቴ ቃለ ጉባኤና ከዉይይት የተረጋገጠ መሆኑ እንዲሁም ከአሸናፊው ዕቃ አቅራቢ ድርጅት ጋር በማሽኖቹ ተከላና አጠቃቀም ዙሪያ ስልጠና እንዲሰጥ ስምምነት ቢኖርም ስልጠናው ያልተሰጠ መሆኑ፣ የህክምና መሳሪያዎቹን ፈትሾ ትክክለኛነታቸውን አረጋግጦ የተረከበው ቡድን በግዢዉ መዘርዝር መሰረት ገቢ ያለሆነን እቃ እንደገባ በማድረግ ማረጋገጫ ከመስጠቱ ባሻገር ለአሸናፊ ድርጅቱ ክፍያ እንዲፈፀም ጥረት የተደረገ መሆኑን እንዲሁም የባዮ ሜዲካ ክፍል ኃላፊ ለጥቅም ግጭት በሚያጋልጥ መልኩ የህክምና መሳሪያዎቹን ትክክለኛነት የመፈተሽ፣ የማረጋገጥ እና የማጽደቅ ተግባራትን ደራርበው መስራታቸው ለሙስና እና ብልሹ አሰራር በር ከፋች መሆኑን በተደረገው አስቸኳይ የማጣራት ስራ ለመረዳት ተችሏል።

ሆስፒታሉ በግዢ ጨረታ አሸናፊ የሆነዉ ድርጅት በጨረታ ሰነድ መዘርዝር (ስፔሲፊኬሽን) መሰረት ገቢ ያልተደረጉትን 4 ፕሮቮች ማለትም Micro curved probe × 2፣endo cavity probe × 2፣ የማሽኑ አጋዥ ቁሶች የሆኑትን ultrasound paper 198 roll፣ አንድ ሊትር ጄል (one liter gel) አሟልቶ እንዲያስገባ ማድረግ እንዳለበት፤ አሸናፊው ድርጅት በግልጽ የጨረታ ግዥ ፍላጎት መዘርዘር(ስፔስፊኬሽን) ስምምነት መሰረት የማሽኑን ገጠማ እና አጠቃቀም ለሚመለከታቸው ባለሙያዎች ስልጠና እንዲሰጥ መመቻቸት እንዳለበት፣ሐመርናሳ ፋርማሲዩቲካልስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር በጨረታ ያሸነፈዉን የአልትራሳዉንድ ማሽን ግዢ በሰነዱ መዘርዝር መሰረት ለማቅረብ የተስማማቸዉን በዉሉ መሰረት ገቢ አድርጎ ሳያጠናቅቅ ክፍያ መፈጸም እንደሌለበት እና አንድ ግለሰብ



የህክምና እቃዎች ፈታሽ፣ አረጋጋጭ እና አጽዳቂ የሆነበት አሰራር ለሙስና፣ ለብልሹ አሰራርና ለጥቅም ግጭት የሚያጋልጥ በመሆኑ ለወደፊቱ አሰራሩ መስተካከል እንዳለበት እንዲሁም የህክምና እቃዎቹ በግልጽ ጨረታ የግዥ ፍላጎት መዘርዝር መሰረት ተሟልተው ሳይቀርቡ ተሟልተው የቀረቡ ናቸው የሚል ማረጋገጫ የሰጡ ፈታሽና አረጋጋጭ (commissioning and/or testing team) አባላት እና አመራር ላይ አስፈላጊውን የተጠያቂነት ስርዓት ለማስፈን አስተማሪ አስተዳደራዊ እርምጃ በመውሰድ በተሰጠው የምክረ-ሀሳብ መሰረት የተደረሰበትን ውጤት ለኮሚሽኑ እንዲያሳውቁ በሚል ምክረ-ሀሳብ ተሰጧቸዋል።

በተጨማሪም ኮሚሽኑ አስቸኳይ የሙስና እና ብልሹ አሰራሮች መከላከል የማጣራት ስራ ያካሄደው ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት መስከረም 22/2015 ዓ.ም በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ባወጣው ክፍት የስራ ማስታወቂያ በድርጅቱ አሰራር መሰረት ቅድሚያ ለውስጥ ሰራተኞች የደረጃ እድገት እና ዝውውር መሰጠት እያለበት ለውጭ የቅጥር ማስታወቂያ እንዲወጣ መደረጉ መመሪያውን የጣሰ ነው በሚል ጥቅምት 04/2015 ዓ.ም በቀረበ የጥቆማ መነሻነት ነው።

የማጣራት ስራው የተከናወነው በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት በአካል በመገኘት ለማጣራት ስራው የሚያስፈልጉ ሰነዶችና ማስረጃዎችን በማሰባሰብና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይት በማድረግ ነው።

በተካሄደው የማጣራት ስራ የውስጥ የደረጃ እድገት ዝውውር ሳይጠናቀቅ እና ውጤቱ በይፋ ሳይታወቅ የውጭ የቅጥር ማስታወቂያ የወጣ መሆኑ፣ ከውጭ በመጡ ባለሙያዎች የህትመት ቴክኖሎጂውን መጠቀም የሚችሉ ሙያተኞች በስራ መደቡ ላይ በፍጥነት ለማሟላት ሲባል የድርጅቱን የሰው ሀብት ሥራ አመራር ልማት መምሪያ መከተል አለመቻሉ እና ለቼክ ፐርሰናላይዜሽን ክፍል በልዩ ሁኔታ ከውስጥ የደረጃ እድገት ጋር በተመሳሳይ ጊዜ ለተመሳሳይ የስራ መደብ የውጭ የስራ ማስታወቂያ እንዲወጣ የተደረገው በማኔጅመንት ውሳኔ እንደሆነ የተገለፀ ቢሆንም የጉዳዩን አስቸኳይነት በተመለከተው ለውስጥ ሠራተኛ ግንዛቤ አለመሰጠት የሚሉ የአሰራር ክፍተቶችን መለየት ተችሏል።

በብርሃን እና ሰላም ማተሚያ ድርጅት የሰው ሀብት ሥራ አመራር ልማት መምሪያ ቁጥር BSCRD-0423.6 የቅጥር አፈፃፀም ቋሚ ቅጥር ከመፈፀሙ በፊት ሊሟሉ የሚገባቸው ሁኔታዎች አንቀፅ 3.6.1.2 ከውስጥ ሰራተኞች በደረጃ እድገት ወይም እንደ አስፈላጊነቱ በዝውውር ለመመደብ ያልተቻለ ከሆነ፤ በድርጅቱ ሰራተኞች ህብረት ስምምነት አንቀፅ 3ለ የድርጅት ግዴታዎች ተራ ቁጥር 27 መሰረት ድርጅቱ የቅጥር ማስታወቂያ ከመውጣቱ በፊት ለድርጅቱ ሠራተኞች የደረጃ እድገት ማስታወቂያ ወጥቶ መስፈርቱን የሚያሟላ ሠራተኛ ካልተገኘ ብቻ የቅጥር ማስታወቂያ የሚወጣ መሆኑን ይገልጻል።

በዚሁ መሰረት የውጭ የቅጥር ማስታወቂያ በአስቸኳይ እንዲወጣ የተደረገበት ዋነኛው ምክንያት ለሚስጥራዊ ህትመት የሚያስፈልግ ማሽን ከውጭ ለማስገባት በልዩ ሁኔታ ተፈቅዶ መሆኑ ቢገለጽም የውስጥ ደረጃ እድገት እና ዝውውር ሂደቱ በተቀመጠው መመሪያ መሰረት ከተጠናቀቀ በኋላ የውጭ የቅጥር ማስታወቂያ እንዲፈፀም ድርጅቱ የራሱን አስተዳደራዊ ማስተካከያ በመውሰድ የተደረሰበት ውጤት ለኮሚሽኑ እንዲያሳውቅ ምክረ-ሀሳብ የተሰጠው መሆኑ ተመላክቷል።

በሌላ መረጃ ኮሚሽኑ በስራና ክህሎት ሚኒስቴር በውጪ ሀገር የስራ ስምሪት አሰራር ስርዓት ዙሪያ በህግና መመሪያ ከተቀመጠው አሰራር ውጪ የጉዞ ሰነድ ሳይሟላ የውል ሰነድ እንዲፀድቅ እየተደረገ መሆኑን በቀረበ ጥቆማ መሰረት አስቸኳይ የሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል ጥናት በማካሄድ የማጣራት ስራን አከናውኗል።

ኮሚሽኑ የማጣራት ስራውን ያከናወነው በሚኒስቴር መ/ቤቱ በአካል በመገኘት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ኃላፊዎች፣ የውል ምዝገባና ማፅደቅ የስራ ኃላፊዎች፣ የስራ ስምሪት ያከናወኑ ተጓዦችን ሰነድና የውጭ ሀገር የስራ ስምሪት አዋጆችን በመመልከት መረጃው እንደተሰበሰበ መረዳት ተችሏል።

ለውጪ የስራ ስምሪት ተጓዦች የሚሰጠውን የቅድመ ጉዞ ገለፃ ስለመውሰዳቸው በሚያሳይ ሰርተፍኬት ላይ ሳይፈረም እንደሚሰራላቸው፣ ለውጪ የስራ ስምሪት የሚያስፈልጉ ሰነዶች ሳይሟሉ ወደፊት እንዲያመጡ እናደርጋለን በሚል ብቻ መሰራቱ፣ አንዳንድ ትክክለኛ ያልሆነ የስራ ምዘና በመጠቀም የውጪ የስራ ስምሪት ውል መፈፀሙና ከተቀባይ ሀገራት ጋር በሚኖረው የሁለትዮሽ ስምምነት መሰረት በአሰሪው ተፈርሞ ስለትክክለኛነቱ የኢፌዲሪ ሚሲዮን እና በውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ መሆን ያለበት ቢሆንም አንዳንድ ይህን ሂደት የማያሟሉ የስራ ውሎች የሚከናወኑ መሆኑን የተደረገው የማጣራት ስራ ውጤት ይጠቁማል።

የሚኒስቴር መ/ቤቱ የውጪ የስራ ስምሪት ተጓዦች ቅድመ ገለፃ ሰርተፍኬት፣ ለሚሰሩት ስራ ተመጣጣኝ ምዘና የወሰዱበት ማስረጃ እና የታደሰ ፓስፖርት፣ የጤና ምርመራ ውጤት የሚያሳይ ማስረጃ፣ ለስራ ሲሄዱ የሚቀበላቸው ተወካይ መኖሩ መረጋገጥ ያለበት መሆኑ፣ በኢትዮጵያ ኢንባሲ እና በውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ የስራ ስምሪት ቪዛ፣ ከፖሊስ የአሻራ ምርመራና ሌሎችንም መረጃዎችን አሟልተው ሲገኙ የስራ ስምሪት ውል ተመርምሮ የሚፀድቅ መሆኑን ቅድመ ሁኔታዎችን ያስቀምጣል።

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለውጪ ሀገር የስራ ስምሪት የሚያስፈልጉ ሰነዶች በግልፅ በመመሪያው ላይ የተቀመጡ ሆነው ሳለ አግባብነት በሌለውና ግልፅ ባልሆነ መልኩ ቀጣይ እንዲያስተካክሉ በሚል ወይም ባለው ሰነድ መነሻነት ይሰራላቸው እየተባለ የሚከናወኑ ተግባራት ብልሹ አሰራርን ከማስፋፋቱም ባሻገር ከበስተጀርባ ለሙስና አመቺ መንገድ የሚከፍት በመሆኑ በሙስና ወንጀሎች አዋጅ 881/2007 አንቀፅ 13 ንዑስ አንቀፅ 1/ለ መሰረት የመንግስት ስራን ያለ አግባብ መምራት፣ አግባብ ባለው ባለስልጣን ወይም ኃላፊ ከተወሰነው በላይ ማናቸውንም ውል የተዋዋለ ወደሚል የሙስና ወንጀል ድንጋጌ የሚወስድ በመሆኑ አሰራር ስርዓቱ በመመሪያው ላይ የተቀመጡትን የትግበራ ሂደት በመጣስ ለውጪ የስራ ስምሪት አንድ ተጓዥ መሟላት ያለበትን ተገቢ ሰነዶች ሳያሟላ እንዲያልፍ በሚያደረጉ የውስጥም ሆነ የውጪ አካላትን በማጣራት፣ በመለየትና ክትትል በማድረግ ተገቢውን የእርምት እርምጃ መውሰድና መስተካከል ያለበት መሆኑን ኮሚሽኑ ምክረ-ሀሳብ ሰጥቷል።

በመጨረሻም ኮሚሽኑ በሐረማያ ዩንቨርሲቲ በሀሰተኛ ማህተም ገንዘብ ማጭበርበር እና የስራ ቅጥር ላይ የቀረበውን ጥቆማ መሰረት በማድረግ አስቸኳይ የሙስና እና ብልሹ አሰራሮች መከላከል የማጣራት ስራ ያካሄደው በዩኒቨርስቲው የግዥ ባለሙያ የሆነው አቶ ግርማ ለገሰ የማህበረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዚዳንት በሆኑት በዶ/ር ይስሀቅ ስምና የስራ ኃላፊነትን የያዘ ህገወጥ/ሀሰተኛ ማህተም በማሰራት በዩኒቨርስቲው ፋይናንስና ሌሎች የስራ ክፍል በሚገኙ ግብረ አበሮቹ ጋር በመሆን ሀሰተኛ ሰነድ በማዘጋጀትና በመፈረም ልዩ ልዩ የውሎ አበል ክፍያዎች እንዲከፈሉ እንዲሁም የተለያዩ ግዥዎች እንደተፈፀሙ ንብረቶቹ ወጪና ገቢ እንደተደረጉ በማስመሰል በግምት ከ50,000,000.00 (ሃምሳ ሚሊዮን)ብር በላይ የሚሆን ክፍያ እንዲከፈል በማድረግ የማጭበርበር ስራ እየሰራ መሆኑን እንዲሁም የዩኒቨርሲቲው አካዳሚክ ም/ፕሬዚዳንት በ2014 ዓ.ም ከዩንቨርስቲው ሲቪል ኢንጅነሪንግ ትምህርት ክፍል የተመረቀ አቶ ኢዮብ መንግስቱ የተባለ ልጃቸውን ለዩኒቨርስቲው ማመልከቻ በመፃፍ ካለምንም ማስታወቂያ ከትምህርት ክፍሉ ፍላጎት ውጭ እንዲሁም የግለሰቡ የትምህርት ውጤት የተሻለ ባልሆነበት ሁኔታ በረዳት መምህርነት እንዲቀጠር ተደርጓል በሚል በቀረበ የጥቆማ መነሻነት የማጣራት ስራ ሲያካሂድ ቆይቷል።

ስራው የተከናወነው በዩንቨርሲቲው በአካል በመገኘት ለማጣራት ስራው የሚያስፈልጉ ሰነዶችና ማስረጃዎችን በማሰባሰብና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይት በማድረግ ሲሆን፣ የዩኒቨርስቲው የግዥ ባለሙያ የሆነው አቶ ግርማ ለገሰ በዩኒቨርሲቲው የማህበረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዚዳንት በሆኑት የዶ/ር ይስሀቅ ስምና የስራ ኃላፊነትን የያዘ ሀሰተኛ ማህተም በማዘጋጀት በራሱ እና በግበረ-አበሮቹ የሂሳብ አካውንት ህጋዊ በማስመሰል አበል ሲቀበል የነበረ መሆኑ፣ ተመሳሳይ የማጭበርበር ተግባር ለመፈጸም ሲሞክር ተደርሶበት በዩኒቨርሲቲው ጥበቃ እና ደህንነት መያዙ፣ ተጠርጣሪዎቹ አቶ ግርማ ለገሰ፣ አቶ ወንድሙ ማሞ እና አቶ እስክንድር ማሽላ በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሀረርጌ ዞን ፖሊስ በቁጥጥር ስር ውለው ተጨማሪ ማጣራት እየተደረገ መሆኑ፣ በዚህም ተግባር የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 ክፍል ሁለት የሙስና ወንጀል ድንጋጌዎች አንቀጽ 23 መንግስታዊ ወይም የህዝባዊ ሰነዶችን አስመስሎ ማዘጋጀት፣ ወደ ሀሰት መለወጥ ወይም በሀሰተኛ ሰነድ መገልገል በሚለው አርዕስት ስር የተዘረዘሩትን በመጣስ የሙስና ወንጀል የተፈጸመ መሆኑን የማጣራት ስራ ውጤት ይጠቁማል።

በሌላ በኩል በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሀገር ውስጥ መምህራን ምልመላ፣ ቅጥር እና ልማት ስርዓት ለመደንገግ የወጣ መመሪያ ቁጥር 01/2011 ገጽ 5 ላይ ከመጀመሪያ ዲግሪ ተመልምለው በረዳት ምሩቅነት ለሚቀጠሩ አካዳሚያዊ አፈጻጸም 35፣ የሚቀጠሩበት ትምህርት መስክ እና የእንግሊዝኛ ቋንቋ የጽሁፍ ፈተና ውጤት 35፣ ቃለ መጠይቅ ለመምህርነት ሙያ ያለው ፍቅር፣ ፍላጎት እና ዝግጅት ጨምሮ የሚታይበት20፣ ከትምህርት ክፍሉ መምህራን የሚሰጥ ምስክርነት(Recommendation) (10)፣ በጠቅላላው ከ100 መመዘኛዎች ተቀምጠው እያለ የአቶ እዮብ መንግስቱ የቅጥር ሂደት ግን በተዘረዘሩት መመዘኛዎች ያላለፉ መሆኑ፣ በሐረማያ ዩኒቨርሲቲ በሲቪል ምህንድስና ምሩቅ የሆኑ ከፍተኛ ነጥብ ያስመዘገቡ ቢኖሩም ዜጎችን እኩል ተወዳዳሪ እና ተጠቃሚ ከማድረግ አኳያ አንድን ምሩቅ ብቻ መልምሎ መቅጠር ተገቢነት የሌለው መሆኑ፣ አቶ እዮብ መንግስቱ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የመቀጠር መብት ያላቸው ቢሆንም ወላጅ አባት የሆኑት የዩኒቨርሲቲው አካዳሚክ ም/ፕሬዚዳንት ልጃቸው እንዲቀጠር በማመልከቻ መጠየቃቸው ግን ግልጽ የሆነ የጥቅም ግጭት የታየበት ሂደት መሆኑ፣ ይህም ተግባር የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 ክፍል ሁለት የሙስና ወንጀል ድንጋጌዎች አንቀጽ 13 የመንግስት ወይም ህዝባዊ ድርጅት ስራን በማያመች አኳኋን መምራት፤ ንዑስ አንቀጽ 4/ሀ ራሱ ወይም የቅርብ ዘመዱ ባለጥቅም በሆነበት ድርጅት የስራ ግንኙነት ውል እንዲፈጸም ያደረገ መሆኑን የተደረገው የማጣራት ስራ ያመለክታል።

በተካሄደው የማጣራት ስራ በዩንቨርሲቲው የተገኙ የአሰራር ክፍተቶች ሁሉም እንዲስተካከሉ ኮሚሽኑ ምክረ-ሀሳብ የሰጠ ሲሆን በዩንቨርሲቲው የሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች የተዘረፈውን የገንዘብ መጠን በማወቅ አስፈላጊውን ተጠያቂነት እንዲሰፍን፣ በትብብር እና በቅንጅት ብልሹ አሰራርን መከላከል እንዲቻል፣ የተካሄደው የቅጥር አፈጻጸም እንደገና ቢታይና በድርጊቱ የተሳተፉ አካላት ላይ አስተማሪ የሆነ አስተዳደራዊ የማስተካከያ እርምጃ ቢወሰድ፣ የበላይ ኃላፊዎች ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ከህግና መመሪያ ባፈነገጠ መልኩ ተፅእኖ እንዳያሳድር ጥንቃቄ ቢደረግ፣ በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሀረርጌ ዞን ፖሊስ እየተከናወነ ለሚገኘው ምርመራ እየተሰጠ ያለው ድጋፍ ተጠናክሮ እንዲቀጥል እና ጊዜ ሳይወስድ ጥፋተኞች አስተማሪ ቅጣት እንዲቀጡ አስፈላጊውን ትብብር የማድረግ ስራ ተጠናክሮ መሰራት እንዳለበት እንዲሁም ዩንቨርስቲው ከላይ በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ የተደረሰበትንም ውጤት ለኮሚሽኑ እንዲያሳውቅ በምክረ ሀሳቡ ተመላክቷል።

# ከሙስና ምርመራ ዘገባ ማህደር



በዚህ ዓምድ የተለያዩ ከሙስናና ብልሹ አሠራር አንፃር በሀገር አቀፍ ደረጃ የተከናወኑና ለህብረተሰቡ ከፍተኛ እውቀትና እውነተኛ መረጃ ይሰጣሉ ተብለው የሚታመኑና በሙስና ወንጀል የተመዘበረውን የሀገር፣ የህዝብና የመንግስት ሀብት በማስመለስ ዙሪያ የተሰሩ ስራዎችንና ግንዛቤ የሚፈጠርበት አጠር ባለ ሁኔታ የሚቀርብ ሲሆን፣ ሀገራችን ያፀደቀቻቸውንና እየተገበረች ያለቻቸውን የተለያዩ ዓለም ዓቀፍ፣ አህጉር ዓቀፍና ቀጠና ዓቀፍ ህጎችና አፈፃፀማቸውን አስመልክቶ የተሰሩና በመሠራት ላይ ያሉ ዋና ዋና ተግባራት አጠር ተደርገው የሚቀርቡበት ነው።

## ከዓለም ዓቀፍ ህጎችና ስምምነቶች አንፃር፤

ውድ አንባቢዎቻችን በጥቅምት ወር ዕትማችን ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግስታት የፀረ-ሙስና ኮንቬንሽን፣ የአፍሪካ ህብረት የፀረ-ሙስና ኮንቬንሽንና የምስራቅ አፍሪካ መንግስታት የጋራ የፀረ-ሙስና መከላከልና መዋጋት ስምምነቶችን ቀድማ ከመፈረምና የህገ መንግስቷ አካል በማድረግ የሰራቻቸውን ተጨባጭ ስራዎች በመጠኑ በማስቃኘት ቀሪውን በዚህ በህዳር ወር ዕትም እንደምናስነብባችሁ ቃል በገባነው መሠረት እነሆ ብለናል።

በጥቅምት ወር እትማችን ፅሁፍ መጨረሻ የነበረው ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግስታት የፀረ-ሙስና ኮንቬንሽን ድንጋጌዎችን በመተግበር ዙሪያ የተለያዩ ስራዎችን መስራቷንና እነዚህንም ስራዎች ሁለት ጊዜ በአባል ሀገራት በማስገምገም የአንደኛውን ዙር የ5 አመት አፈፃፀም ግምገማ ግብረ መልስ ተቀብላ እየተገበረች መሆኑንና የሁለተኛውን ዙር የ 5 አመት ሪፖርት ለድርጅቱ ዋና ፅ/ቤት ኦስትሪያ ቬይና በመላክ በቀጣይ ሪፖርቷን በአካል እንዲገመግሙ ለተመረጡት ግሪክና ኮንጎ ብራዛቢል በአካል በዚህ ዓመት 2015 ዓ.ም መምጣታቸውን እየተጠባበቀች ትገኛለች የሚል ነበር።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ሀገሪቱ የገባቻቸውን ግዴታዎች በተጨባጭ በመተግበር ዙሪያ በጣም ሰፊ ስራዎችን ሰርታለች በመስራትም ላይ ትገኛለች። አንዱና የሚጠቀሰው ዋና ስራ የኮንቬንሽኖቹ ስራዎች በስፋት የሚሰሩት ከኮሚሽኑ ውጭ ባሉ ተቋማት በመሆኑና የኮሚሽኑ ዋና ተግባር ሀገራዊ የፀረ-ሙስና ትግሉን የክልል መንግስታትን ጨምሮ በበላይነት ማስተባበር በመሆኑ፣ የኮንቬንሽኑ አፈፃፀም በጋራ የሚገመግም የተለያዩ ተቋማት ሀላፊዎች በበላይነት የሚከታተሉትና ከነዚህ ተቋማት በተውጣጡ ባለሙያዎች የተደራጀ ሀገራዊ የቴክኒክ ኮሚቴ ተዋቅሮ የሀገሪቱን ዝርዝር አፈፃፀም እየተከታተለ የሚያስፈፅና የየአምስት አመት አፈፃፀሟንም ዝርዝርና ዓለም ዓቀፍ ስታንደርድ መሠረት እያዘጋጀ ለመንግስትና ለኮንቬንሽኖቹ ዋና ፅ/ቤት እየላከ የሚያስገመግም ሲሆን፣ ከግምገማው በመነሳት የሚሰጡ ግብረ መልሶችንም አንድ በአንድ እየተከታተለ በማስፈፀም አጠናቅቆ ሪፖርት ያደርጋል። የመጀመሪያውን ዙር ግምገማ የተሠጡ 31 የሚሆኑ ግብረመልሶችን አተገባበር ባሁኑ ሰዓት እየተከታተለ ሲሆን የ2ኛ ዙር የ5 ዓመት አፈፃፀምንም ዝርዝር ሪፖርት ለድርጅቱ ዋና ማስተባበሪያ ፅ/ቤት የላከው ይሄው ሀገራዊ የቴክኒክ ኮሚቴ ነው።

ሀገራችን ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸውን ኮንቬንሽኖች በተጨባጭ ለመተግበር እጅግ ሠፊ እርምጃዎችን የወሰደች ሲሆን በህጋዊ ማዕቀፍና በተቋማዊ አደረጃጀት በኩል የወሰደቻቸውን ተጨባጭ እርምጃዎች በዚህ ወር ጋዜጣ ዕትማችን እንደሚከተለው እያቀረብን ቀሪ ትንታኔዎችን በቀጣይ ወር የምንቀጥል ይሆናል።

## ከህግ ማዕቀፍ አንፃር፤

ከላይ እንደተገለፀው ሀገራችን ኢትዮጵያ ሶስቱንም የስምምነት ሠነዶች ቀድማ በመፈረምና በማፅደቅ ወደ ተግባር ስራ የገባች ሲሆን ለዚህ ደግሞ ማስፈፀሚያ የሚሆኑ የተለያዩ ህጎችን አዋጆችን ደንቦችን መመሪያዎችንና የፖሊስ ሠነዶችን በማዘጋጀት ጠንካራ ስራ እየሰራች የምትገኝ ሲሆን፣ የሚከተሉትን ለዓብነት ማየት እንችላለን።

- በፌደራል ህገ መንግስቷ አንቀፅ-9(4) እና አንቀፅ-13 ላይ ኮንቬንሽኖቹ የሀገሪቱ የበላይ ህግ የሆነው የፌደራል ህገ መንግስት አካል መሆኑን የደነገገች መሆኑ፤
- በህገ መንግስቱ ድንጋጌ መሠረት ለመተግበር አዋጅ ቁጥር-544/2007 (2000) ዓ.ም እና አዋጅ ቁጥር 545/2007 ዓ.ም ያወጣች መሆኑን፤
- ብዛት ያላቸው የማስፈፀሚያ ህጎችን አዋጆችን መመሪያዎችን ያወጣች መሆኑን፤
- የፌደራል ስነምግባርና የጸረሙስና ማቋቋሚያ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1236/2021 (2014)፤
- የሀብት ማሳወቅና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር .668 /2010(2003)፤
- የተሸሻላው የጸረሙስና ልዩ የመረጃ አቀራረብ አሰራር መመሪያ አዋጅ ቁጥር 882/2015 (2008)፤
- የጠቋሚዎችና የምስክሮች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር699/2010 (2002)፤
- የፌደራል የሲቪል ሰርቪስ ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር.1064/ 2017.(2010)፤
- የህገወጥ የገንዘብ ዝውውርና የሽብርተኞችን በገንዘብ መደገፍን የመከላከልና የማስወገድ አዋጅ ቁጥር. 780/2013 (2006)፤
- የኢፌዲሪ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት ተገባርና ሀላፊነት አዋጅ ቁጥር . 1263 / 2021(2015)፤
- የፌደራል ፍርድቤቶች አዋጅ ቁጥር .1234/ 2021(2015)፤
- የኢትዮጲያ ወንጀለኞች የፍትህ ፖሊሲ Criminal March 4,2011(2004)፤
- የክልሎች የስነምግባርና የጸረ ሙስና መከታተያ ክፍሎች ማቋቋሚያ አዋጅ፤
- የክልሎች የሀብት ማሳወቅና ምዝገባ አዋጆች፤
- የመንግስት የልማት ድርጅቶች የስነምግባር መከታተያ ክፍሎች መመሪያ ቁጥር.20/2021፤
- የግል/የህዝባዊ ድርጅቶች የስነምግባር መከታተያ ክፍሎች መመሪያ ቁጥር-23/2015. (23/2021)፤

ከላይ ከተጠቀሱ ህጎች አዋጆች ደንቦችና መመሪያዎች በተጨማሪ የተለያዩ የፖሊሲ ሠነዶችን በማዘጋጀትና በማፅደቅ እየተገበረች ሲሆን የሚከተሉትን ለዓብነት ማየት እንችላለን።

ብሄራዊ የተቀናጀ የወንጀል መከላከል ስትራቴጂ ሠነድ፤ የተቀናጀ የተቋማት የሙስና መከላከል ስትራተጂ ሠነድ፤ ብሄራዊ ስትራተጂክ እቅድ ሠነድ፤ የኢትዮጲያ የትምህርት ልማት ፖሊሲ ሠነድ፤ የህዝብና የመንግስት አገልግሎት ሰጪ ፖሊሲ ሠነድ፤ ብሄራዊ የጸረ ሙስና ፖሊሲና ስትራተጂ ሠነድ፤ ብሄራዊ ህገ ወጥ የገንዘብ ዝውውርና የጸረ ሽብርተኝነት መከላከል ፖሊሲ ሠነድ፤ የወንጀል ፍትህ ፖሊሲ ሠነድ፤ የኢትዮጲያ ብሄራዊ የጸረ ሙስና ሰርቬይ ጥናት ሠነድ የሚጠቀሱ ናቸው።

## የተለያዩ ተቋማትን ከማቋቋምና ከማደራጀት አንፃር፤

ከላይ እንደተገለፀው ሀገራችን ኢትዮጵያ ሶስቱንም የስምምነት ሠነዶች ቀድማ በመፈረምና በማፅደቅ ወደ ተግባር ስራ የገባች ሲሆን ለዚህ ደግሞ ማስፈፀሚያ የሚሆኑ የተለያዩ ህጎችን፣ አዋጆችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን እንዲሁም የፖሊስ ሠነዶችን ከማዘጋጀት በተጨማሪ የወጡ ህጎች የሚተገበርባቸውን የተለያዩ ተቋማትን በማቋቋም ግዴታዋን እየተወጣች የምትገኝ ሲሆን የሚከተሉትንም ለዓብነት ማየት እንችላለን።

- የፌደራል የሥነ ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን መቋቋም፤
- የክልሎች የሥነ ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች መቋቋም፤
- በመንግስት መስሪያ ቤቶችና በመንግስት ልማት ድርጅቶችን በህዝባዊ ድርጅቶች ተቋማት የስነ

ምግባር መከታተያ የስራ ክፍሎች መቋቋማቸው፤

- የሙስና ወንጀልን የሚመረምር ራሱን የቻለ የምርመራ ስራ ክፍል የተቋቋመ መሆኑ፤
- የሙስና ወንጀልን የሚከስ ራሱን የቻለ የዓቃቤ ህግ ስራ ክፍል የተቋቋመ መሆኑ፤
- የሙስና ወንጀልን ብቻ የሚከታተሉና ፍርድ የሚሠጡ የተለያዩ የፍርድ ቤት ችሎቶች መቋቋማቸው፤
- እነዚህ አደረጃጀቶች በሁሉም የክልል የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች በተመሳሳይ ሁኔታ የተደራጁ መሆኑ
- ሌሎች ያልተጠቀሱም አደረጃጀቶች ይገኛሉ።

የሙስና ወንጀል ድርጊት የተለያዩ መነሻዎች መሰረት በማድረግ ወይም የተለያዩ ዓላማዎችን ለማሳካት ሊፈፀም የሚችል ሲሆን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ማግኘት አንዱ ነው። ከዚህ የተነሳ አንድ የሙስና ወንጀል አድራጊ ከሙስና ወንጀል ድርጊት ያገኘውን ሀብት እንዲጠቀም መደረግ የለበትም የሚለው የህግ መርህ ስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል። የዚህ መርህ ሌላ መገለጫ የሆነው ከሙስና ወንጀል ድርጊት የተገኘው ሀብት ወደ ነበረበት ተመላሽ ተደርጎ የሙስና ወንጀሉ ተጎጂ እና አጠቃላይ ኢኮኖሚው እንዳይጎዳ ማድረግ ነው። ስለዚህ የሀብት ማስመለስ ተግባር የሚያተኩረው ማንም ሰው ከሙስና ወንጀል ድርጊቱ የገንዘብ ጥቅም እንዳያገኝ ማድረግ ነው።

በፍትህ ሚኒስቴር በተካሄደ የሙስና ወንጀል ምርመራ 49,868,465.44 ብር፣ 2 ተሽከርካሪዎች እና አጠቃላይ የዋጋ ግምታቸው 119,000 የአሜሪካን ዶላር የሆኑ 17 ኮንቴነሮች በመንግስት እንዲወረሱ መደረጉን እና 7,891 መዛግብት በፖሊስ ምርመራቸው ተጣርቶ የቀረቡ ሲሆን በ7,789 መዛግብት ላይ የተለያዩ ውሳኔዎች በዐቃብያነ ሕግ መሰጠቱ ተመላክቷል። በተያያዘም በተደራጁና ድንበር ተሻጋሪ፣ በሙስና እና በኢኮኖሚ ወንጀል ዓይነቶች በአጠቃላይ 1,112 የምርመራ መዝገቦች በዐቃብያነ ህግ እጅ የነበሩ ሲሆን ከእነዚህ መካከል በ693 መዝገቦች ላይ በዐቃቤ ህግ የተለያዩ ውሳኔዎችን ተሰጥቶባቸዋል።

በልዩ ልዩ የወንጀል ጉደዮች 18,412 መዝግብ ላይ በቀጥታ ክስ ቀርቦ ክርክር የተደረገባቸው ሲሆን ከእነዚህ መዛግብት ውስጥ 3,657ቱ በፍርድ ቤት ውሳኔ ሲያገኙ በ3,541 መዛግብት ላይ ዐቃቤ ሕግ በከሳሾች ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ እና ቅጣት እንዲጣል ማድረግ ችሏል፤ ክስ ከቀረበባቸው 23,647 ተከሳሾች ውስጥም ፍርድ ቤት በ7,976 ተከሳሾች ላይ ውሳኔ የሰጠ ሲሆን ከነዚህም መካከል በ7,819 ተከሳሾች ላይ የቅጣት ውሳኔ መተላለፉን አቶ በረከት ገልጸዋል።

በተደራጁ የኢኮኖሚና የሙስና ወንጀል ዓይነቶችም ባለፉት ሶስት ወራት በ1,585 የክስ መዝገቦች ላይ ክርክር ተደርጎባቸው በ262 መዝገቦች በፍርድ ቤት ታይተው ውሳኔ የተሰጠባቸው ሲሆን በ245ቱ ላይ የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሳኔ መሰጠቱን ኃላፊው አብራርተዋል። በሌላ በኩል በህገ ወጥ የሰዎች አዘዋዋሪዎች ላይ ተገቢውን ምርመራ በማድረግ 16 መዝገቦች ላይ ክስ ተመስርቶ ክርክር ላይ ያለ ሲሆን ወንጀለኞች በ3 መዛግብት እስከ 16 ዓመት ድረስ እንዲቀጡ ተደርገዋል።

በአገሪቱ በተለያዩ ስፍራዎች በነበሩ ግጭቶች የተፈጸሙ ወንጀሎችን የሚመረምር የምርመራ ቡድን በማዋቀር በሁሉም ቦታዎች ምርመራ በማደረግ የተፈጸሙ የሙስና ወንጀሎችን፣ ወንጀል ፈጻሚዎችን እና የወንጀሉን አፈፃፀሙን ሂደት ማጣራትና ክስ የመመስረት ስራ በመስራት ወንጀል ፈፃሚዎችን ተጠያቂ የማድረግ ስራዎች ባለፉት ሶስት ወራት መከናዎናቸውን ጠቁመዋል።

የሙስና ወንጀሎችን የተመዘበሩ የህዝብና የመንግስት ሐብት ከማስመለስ አኳያም ባለፉት ሶስት ወራት በተለያዩ ወንጀሎች የተሳተፉ ወንጀለኞች ንብረት ለይቶ እንዲታገዱ በማድረግ በሕጋዊ መንገድ እንዲመለሱ ማድረግ መቻሉን፤ በዚህም በተለያዩ አምስት ጉዳዮች ብር 49,868,465.44፣ የዋጋ ግምታቸው 2.5 ሚሊዮን ብር የሚያወጡ 2 ተሽከርካሪዎች እና የአንዱ የዋጋ ግምት 7000 ዶላር የሚያወጣ 17 40 ፊት ኮንቴነሮች በመንግስት እንዲወረሱ መደረጉን ከፍትህ ሚኒስቴር ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

በሌላ መረጃ በአማራ ክልል ፖሊስ ኮሚሽን የሙስና ወንጀል ምርመራ መምሪያ ኀላፊ ኮማንደር አግራሩ አሊ እንዳሉት አንድ ግለሰብ ከሙስና ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በአካል፣ በስልክና በኢሜል ጥቆማዎችን ማቅረብ ይችላል።

የሙስና ምርመራ ከዚህ በፊት በጸረ-ሙስና ቢሮ በኩል ሲጣራ እንደነበር ያነሱት መምሪያ ኀላፊው ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ በአዋጅ ቁጥር 263/2012 መሠረት የምርምራ ሂደቱን በፖሊስ፣ የመክሰስ ስልጣንን ደግሞ በአቃቢ ሕግ በኩል እንዲካሄድ መደረጉን ገልጸው፣ የሚሰጡ ጥቆማዎች በፖሊስ በኩል ወደ አንድ ቋት እንዲገቡ ተደርጎ በትክክል የሙስና ወንጀል መኾናቸው ይጣራል፤ ጥቆማው የሙስና ወንጀል መኾኑ ከተረጋገጠ ወደ ምርመራ ይገባል። በዚህም መሠረት የሙስና ጉዳይ ለፖሊስ በአዋጅ ከተሠጠው ጀምሮ ጥቆማዎችን ተቀብሎ የምርመራ ሥራ እያከናወነ መኾኑን ገልጸዋል።

በ2015 ዓ.ም በመጀመሪያዎቹ ሶስት ወራት 24 ጥቆማዎች ቀርበው «በትክክል ወንጀል ተፈጽሞባቸዋል» ተብሎ ምርመራ እየተደረገባቸው ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ደግሞ ሰባቱ ጉዳዮች ተጣርተው ወደ አቃቢ ሕግ ተልከዋል። ጥቆማ የሰጡ የኅብረተሰብ ክፍሎችም በአዋጅ ቁጥር 699/2003 በፍትህ ቢሮ በኩል ከለላ ይደረግላቸዋል።

ከለላ የሚደረገው ጥቆማ አቅራቢው የሰጠው ጥቆማ ተጣርቶ አቃቢ ሕግ ክስ ሲመሰርትና በክርክር ላይ ሲኾን፣ ጥቆማ አቅራቢውም በፍርድ ቤትና በፖሊስ ላይ ቀርቦ የመሰከረ መኾኑ ሲረጋገጥ እንደኾነ ነው። የተሰጠውን ከለላም ፖሊስ ያስፈጽማል። ከለላውም ጥቆማ አቅራቢው በሚያቀርበው የድጋፍ ጥሪ ፈጥኖ በመድረስ ወይንም ከአካባቢው የጸጥታ አካል ጋር የቅርብ ግንኙነት በመፍጠር በሚደረግ ጥበቃ አማካኝነት ሊኾን ይችላል።

በዚህ መሰረት ማኅበረሰቡ ሙስና በሀገር ላይ አደጋው ከባድ መኾኑን ተገንዝቦ ያየውንና የሰማውን ለፖሊስ ኮሚሽን ወይንም ለኮሚሽኑ የሙስና ወንጀል የምርመራ ዘርፍ በአካል፣ በስልክ እና በኢሜል ጥቆማዎችን በመስጠት የተጀመረውን የጸረ ሙስና እንቅስቃሴ ውጤታማነት ማረጋገጥ ይገባል።

በሌላ መረጃ ለሚሰጠው መንግሥታዊ አገልግሎት 3.5 ሚሊዮን ብር ጉቦ ጠይቆ 1.5 ሚሊዮን ብር የተቀበለው ባለሙያ በቁጥጥር ሥር ውሎ ምርመራ እየተደረገበት መሆኑን የአዲስ የአበባ ፖሊስ አስታወቀ።

በቂርቆስ ክፍለ ከተማ የመሬት ሊዝ ባለሙያ የሆነው አቶ ፋሲል አወቀ በቁጥጥር ስር የዋለው ኅዳር 23 ቀን 2015 ዓ.ም መሆኑ ገልፀው፣ ባለሙያው የመኖሪያ ቤት ገዝቶ ካርታውን በስሙ ለማዛወር ከሄደ አገልግሎት ፈላጊ ግለሰብ ኃላፊነቱን ተገን አድርጎ "ቤቱ እግድ አለበት፣ እግዱን አስነስቼ ነፃ ካርታ እሰጥሃለሁ" በማለት 3.5 ሚሊዮን ብር ጉቦ እንዲሰጠው መጠየቁን የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን መረጃን ጠቅሶ ኤፍቢሲ ዘግቧል።

አገልግሎት ፈላጊውም 1.5 ሚሊዮን ብሩን በተጠርጣሪው የግል አካውንት ካስገባለት በኋላ ተጨማሪውን 2 ሚሊዮን ብር እንዲያስገባለት ሲጠይቀው የግል ተበዳይ ጉዳዩን ለፖሊስ አሳውቋል።

ፖሊስም ተጠርጣሪውን ይዞ ምርመራው መቀጠሉን እና የግል ተበዳይ በተጠርጣሪው አካውንት 1.5 ሚሊዮን ብር ገቢ ማድረጋቸው በምርመራ መረጋገጡን የአዲስ ፖሊስ ገልጿል።

ኅብረተሰቡ ማንኛውንም የመንግሥት አገልግሎት ለማግኘት በሚሄድበት ወቅት ጉቦ ሲጠየቅ ለሚመለከተው አካል ጥቆማ መስጠት እንዳለበት ኮሚሽኑ አሳስቧል።

በተመሳሳይ ሁኔታ በሀሰተኛ መታወቂያ የወጣ የሽያጭ መመዝገቢያ ማሽን በመጠቀም ግብይት ሳይኖር ከ29 ሚሊዮን ብር በላይ ግብይት የፈፀሙ በማስመሰል ሀሰተኛ ደረሰኝ የሰጡ ሁለት ግለሰቦች እና በህገወጥ ተግባሩ ላይ ተሳትፎ የነበረው አንድ ግለሰብ በእስራት መቀጣታቸውን የአዲስ አበባ ፖሊስ አስታውቋል።

ተከሳሽ ተስፋሁነኝ ተሾመ ሐምሌ 24/2013 ዓ.ም በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 06 ልዩ ቦታው ቁራ ዳውን ታውን ህንፃ አካባቢ በሚገኝ ንግድ ቤት ውስጥ በሀሰተኛ መታወቂያ የወጣ የሽያጭ መመዝገቢያ ማሽን በመጠቀም ግብይት ሳይኖር 17 ሚሊዮን 940 ሺ ብር ሃሰተኛ ደረሰኝ ቆርጦ ሲሰጥ እጅ ከፍንጅ ተይዟል።

በተመሳሳይ ገነት ሀይሉ በልደታ ክ/ከተማ ባልቻ ሆስፒታል አካባቢ ከሚገኝ አህመድ ህንጻ ውስጥ በሀሰተኛ መታወቂያ በወጣ የግብይት ማሽን ግብይት ሳይኖር 12 ሚሊየን 135 ብር ግብይት እንደተፈፀመ በማስመሰል ሃሰተኛ ደረሰኝ ቆርጣ ስትሰጥ እጅ ከፍንጅ ተይዛለች።

ተከሳሽ ተስፋሁነኝ ተሾመ በፈፀመው ሀሰተኛ ወይም አሳሳች መግለጫ በማቅረብ እንዲሁም ሀሰተኛ ደረሰኞችን ለማዘጋጀትና ለማተም የሚያገለግሉ ማሽኖችን ይዞ በመገኘቱ፤ ተከሳሽ ገነት ሀይሉ በሀሰተኛ መታወቂያ ስም የወጣ የሂሳብ መመዝገቢያ ማሽን በመጠቀም ግብይት ሳይኖር ሃሰተኛ ደረሰኝ ቆርጣ በመስጠቷ በተጨማሪም ተከሳሿ ምንም አይነት የሽያጭ መመዝገቢያ ለመጠቀም የሚያስችል ህጋዊ ፍቃድ እና ሰነድ ሳይኖራት በሀሰተኛ መታወቂያ ስም የወጣ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ይዛ በመገኘቷ ማሽኑን ተጠቅማ ሀሰተኛ ወይም አሳሳች መግለጫ በማቅረቧ ወይም ደረሰኝ አዘጋጅታ በመስጠቷ ሁለቱም ግለሰቦች በፈፀሙት ተደራራቢ ወንጀሎች እንዲሁም ሦስተኛ ተከሳሽ አብዲ ጃቢር ለራሱ ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ ሃሰተኛ ደረሰኝ እንዲቆረጥ በመደለል ያመቻቸ በመሆኑ ክስ ተመስርቶባቸው ጉዳያቸው በፍርድ ቤት ሲታይ ቆይቷል።

የሦስቱን ግለሰቦች ጉዳይ ሲመለከት የቆየው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 11ኛ ወንጀል ችሎት ተስፋሁነኝ ተሾመ በ 14 ዓመት ጽኑ እስራትና በ360 ሺ ብር እንዲሁም ገነት ኃይሉ በ12 ዓመት ጽኑ እስራትና በ210 ሺ ብር የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ሲወስን በአብዲ ጃቢር ላይ የ3 ዓመት ጽኑ እስራት የቅጣት ውሳኔ አስተላልፏል።

በተጨማሪም በኦሮሚያ ክልል ባለፉት ሶስት ወራት ከሙስና ወንጀል ጋር በተያያዘ 1 ሺህ 321 ሰዎች ተከሰው ውሳኔ እንደተላለፈባቸው የኦሮሚያ ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ቢሮ ያሳወቀ ሲሆን፣ ውሳኔ የተሠጠባቸው ተከሳሾች ከአመት ከስድስት ወር እስከ 16 አመት የተፈረደባቸው ሲሆን፥ 230 ሺህ 554 ካሬ ሜትር መሬት ወደመሬት ባንክ ገቢ መደረጉንም ነው ያስታወቀው። በተጨማሪም 70 ሚሊየን ብር፣ ሶስት መኪና እና ሶስት ዘመናዊ ቤቶች ለመንግስት ገቢ መደረጋቸውን የኦ ቢ ኤን ዘገባ ያመላክታል።

በአሁኑ ሰአት ከሙስና ወንጀል ጋር በተያያዘ 285 መዝገቦች በምርመራ ላይ እንደሚገኙ ተገልጿል። የኦሮሚያ ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ቢሮ ሃላፊ አቶ ጉዮ ዋሪዮ ከ289 ሺህ ካሬ ሜትር በላይ መሬት፣ በተለያዩ ባንኮች የሚገኙ 67 ሚሊየን ብር እና ሠባት ቤቶች እግድ ተላልፎባቸው በምርመራ ላይ እንደሚገኙ ገልጸዋል።

በሙስና ወንጀል ተጠርጥረው ምርመራ እየተደረገባቸው ካሉ አካላት መካከል የመንግሥት ባለስልጣናት፣ መሃንዲሶች፣ የመንግስት ሠራተኞች፣ ደላሎችና ባለሃብቶች እንደሚገኙበት ፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት ዘግቧል።

ሌላው መረጃ በኢትዮጲያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን የኦሮምኛ ዝግጅት ክፍል ሀላፊ በላቸው ጀቤሳ እና 2ኛ ተከሳሽ አለማየሁ ቂጥሶ የሙስና ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣውን አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 10 (1) እና 2 ን ተላልፈው በፈጸሙት የሙስና ወንጀል በኢ.ፌ.ድ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ዘርፍ የሙስና ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዐቃቤ ህግ መጋቢት 9 ቀን 2014 ዓ/ም በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የልደታ ምድብ 4ተኛ የሙስና ወንጀል ችሎት ክስ መስርቶባቸው ነበር።

የዐቃቤ ህግ የክስ መዝገብ እንደሚያስታው ተከሳሾች የሸገር ውሀ ባለቤት ዶ/ር ሀሰን መሀመድ ጋር 2ኛ ተከሳሽ ስልክ በመደወል በአዳማ ከተማ ከአንድ ሱቅ የገዛው የታሸገ የሸገር ውሀ ሶፍት መሰል ባዕድ ነገር ቆሻሻ እንዳገኘበት ለኢትዮጵያ ብሮድካስት ኮርፖሬሽን ጥቆማ መስጠቱን ገልጾ በቴሌቪዥን ጣቢያው የኦሮምኛ ዝግጅት ክፍል ኃላፊ የሆኑትን 1ኛ ተከሳሽን አናግሩት በማለት የኃላፊውን ስልክ ቁጥር ለባለሀብቱ ይሰጠዋል።

ባለሀባቱም በተባለው ስልክ በመደወል 1ኛ ተከሳሽን በአካል ሲያገኘው በምስል የተደገፈ ጥቆማው ለክፍሉ እንደደረሰው ለባለሀብቱ በመግለጽ ጉዳዩ በሚዲያው እንዳይተላለፍ ከፈለጋችሁ 500 ሺ ብር ጉቦ እንዲከፍሉ በመደራደር በሌላ ቀን ተከሳሾች ከባለሀብቱ እጅ 100 ሺህ ብር በጥሬ ገንዘብ እንዲሁም ቀሪ 400 ሺህ ብር ደግሞ በ3 ቼኮች ተቀብለው 1ኛ ተከሳሽ መኪና ውስጥ እንዳሉ ባለሃብቱ አስቀድሞ ለፖሊስ በሰጠው ጥቆማ መሰረት የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን አባላት ክትትል ሲያደርጉ ቆይተው እጅ ከፍንጅ በቁጥጥር ስር በማዋላቸው ዐቃቤ ህግ ክስ መስርቶ በሰው እና በሰነድ ማስረጃዎች የተባለውን ድርጊት ተከሳሾች መፈጸማቸውን በበቂ ሁኔታ አረጋግጧል።

በዚሁም መሰረት ፍርድ ቤቱ ሐምሌ 4 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት ዐቃቤ ህግ ባቀረበባቸው ከባድ የጉቦ መቀበል የሙስና ወንጀል ተከሳሾችን እንዲከላከሉ ብይን በሰጠው መሰረት ተከሳሾች የዐቃቤ ህግ ክስ እና ማስረጃ ለማስተባበል የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎችን ለፍርድ ቤቱ አቅርበው ተከራክረዋል።

ክርክሩን የመራው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የልደታ ምድብ 4ተኛ የሙስና ወንጀል ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ተመልክቶ በሰጠው የጥፋተኝነት ፍርድ ምንም እንኳን ዐቃቤ ህግ ተከሳሾች 500 ሺ ብር ጉቦ ተቀብለዋል በማለት በከባድ የሙስና ወንጀል አንቀጽ የከሰሰ ቢሆንም ተከሳሾቹ በቁጥጥር ስር ሲውሉ የ400 ሺህ ብር ቼክ መቀበላቸውን በሚመለከት ቼኩ ላይ የተጻፈው የክፍያ ጊዜ ያለፈበት እና ለክፍያ ቢቀርብም ጥቅም ላይ የማይውል ነው በማለት ተከሳሾቹ በጉቦ ከተቀበሉት የ 500 ሺ ብር ውስጥ ያገኙት ጥቅም በጥሬ ገንዘብ የተቀበሉት 100 ሺህ ብር ብቻ ነው በማለት ዐቃቤ ህግ ክስ ከመሰረተበት የሙስና ወንጀል አዋጅ ቁጥር 881/2008 አንቀጽ 10 ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 ውስጥ በንኡስ 1 ስር ብቻ ጥፋተኛ በማለት ተከሳሾች እያንዳንዳቸው በ 1 ዓመት ከ 6 ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጡ በመወሰን 2ኛ ተከሳሽ የተጣለበት የእስራት ቅጣት በፈተና ጊዜ እንዲገደብለት ወስኗል።

ዐቃቤ ህግ በውሳኔው ላይ ይግባኝ የሚጠይቅ ሲሆን የክርክር ሂደቱን ተከታተልን መረጃ የምናደርሳችሁ ይሆናል ሲል የኢፌዴሪ ፍትህ ሚኒስቴር መረጃውን አጋርቷል።

# ኪነ-ጥበብ

## “የሰርቆ አደሮች” ስብሰባ

ሰሞኑን በአዲስ አበባ አንድ ትልቅ የስብሰባ አዳራሽ ውስጥ የአዲስ አበባ ደረጃ አንድ ሌቦች ስብሰባ አድርገው ነበር። የስብሰባው መሪ ቃል ‹የሕዝቡን ጥያቄ ለመመለስ ሌቦች ምን ሊያደርጉ ይችላሉ?› የሚል ነው። ስብሰባው እንደተጀመረ አንደኛው የታወቀ ሌባ እጁን አወጣና ‹መፈክሩ ላይ የተጠቀስንበት ስም ትክክል አይደለም። ገጽታችንን የሚያበላሽ ነው› ሲል አስተያየት ሰጠ። ጭብጨባ አዳራሹን ሞላው።

‹ታድያ ምን ይሁን፤ መቼም ሌባ መሆናችን ርግጥ ነው› አሉ ሰብሳቢው።

‹ጠየም አድርጉት፤ እንደ ባለጌ ጥሬ ድርግም አይደረግም› አሉ ሌላ አስተያየት ሰጭ።

‹እኮ ምን እንባል› አሉ ሰብሳቢው።

‹ሌሎቹ ሠርቶ አደር፣ አርብቶ አደር፣ ወቶ አደር፣አርሶ አደር ከተባሉ እኛም ‹ነጥቆ አደር› ነው መባል ያለብን›

ይኼው ጻደቀ።

‹የሕዝቡ ምሬት ጨምሯል። ሕዝቡ በሌቦች መማረሩን በተደጋጋሚ እየገለጠ ነው። አንድ ቀን መሣሪያ ቢያጣ እንኳን አካፋና ዶማ ይዞ መነሣቱ አይቀርም።

ከተንተከተከ እሳቱ ጨምሮ

ክዳኑን ይገፋል የፈላበት ሽሮ

ሲባል አልሰማችሁም። ያን ጊዜ ደግሞ ለሁላችን መግቢያ ቀዳዳው ጠባብ ነው የሚሆነው። ለዚህ ጉዳይ እኛው ራሳችን መፍትሔ ማምጣት አለብን› አሉ ሰብሳቢው።

‹ስንናገር ለይተን መናገር አለብን። ሌባ ሁሉ አንድ ዓይነት አይደለም። ኩሩ ሌባና ልክስክስ ሌባ፤ ጨዋ ሌባና ባለጌ ሌባ፤ ሽቃጭ ሌባና ኢንቨስተር ሌባ፤ ነጥቆ ሂያጅና ነጥቆ ገንቢ፤ ገፋፊ ሌባና ለካፊ ሌባ፣ እየተባለ የሚዘረዘር ብዙ ዓይነት ሌባ ነው ያለው። በስመ ሌባ ሁላችንም መሰደብ የለብንም› አሉ አንድ የታወቁ ሌባ።

ሰብሳቢው የተገረሙ ይመስላሉ፤ አገጫቸውን በእጃቸው ይዘው ‹እኔም የእናንተን ያህል ባይሆንም መቼም በዚሁ ስም ተጠርቼበታለሁ። አሁን የዘረዘርከው ግን ምንድን ነው?› አሉት።

ሰውዬው ዕውቀት በመጠየቁ ወንበሩ ላይ ተገላብጦ ተቀመጠና፣ ጉሮሮውን ጠራርጎ ‹መቼም ዕውቀት ማካፈል ደስ ይለኛል። ኩሩ ሌባ ማለት ከሚሊዮን በታች የማይነካ፤ ዝም ብሎ በመቶውም በሺውም የማይልከሰከስ ነው። ልክስክስ ሌባ ደግሞ የዚህ ተቃራኒ ነው። ጨዋ ሌባ ማለት ደግሞ ሲሰርቅ በሕጉ መሠረት የሚሰርቅ ማለት ነው። ሰነድ አዘጋጅቶ፣ ጨረታ አጫርቶ፣ ማስታወቂያ አሠርቶ፣ ቃለ ጉባኤ አያይዞ፤ ዕቃ ገቢ አድርጎ የሚሰርቅ ማለት ነው። ባለጌ ሌባ ደግሞ የዚህ ተቃራኒ ነው። ኢንቨስተር ሌባ ገንዘብ የሚቦጭቀው ከትላልቅ ኢንቨስትመንቶች ብቻ ነው። መጉመድ እንጂ መጉረስ የማያውቅ ቆፍጣና። መጉረድ እንጂ መቁረጥ ያልለመደ ጀግና፤ መቦጨቅ እንጂ መንጨት የማያውቅ ሆደ ሰፊ ማለት ነው።

ሽቃጭ ሌባ ግን ከገቢውም፣ ከወጭውም፣ ከሱቁም፣ ከኅብረት ሱቁም የሚቀነጣጥብ ቀነጣጣቢ ነው። ነጥቆ ሂያጅና ነጥቆ ገንቢ ስለሚባሉት የሌባ ዓይነቶች በደንብ መግለጥ አለብኝ። ‹ነጥቆ ሂያጅ ሌባ› ማለት ካገኘ በኋላ እዚህ ሀገር የማይቀመጥ ሌባ ነው። ይኼ ዓይነቱ ሌባ ለሀገሪቱ ዕድገት ዕንቅፋት ነው። የሀገርን ገቢ ወደ ባዕድ ሀገር የሚያሸሽ ከሐዲ ሌባ ነው። የሀገር ፍቅር ስሜት ፈጽሞ የሌለው ሌባ ነው። እዚሁ ነጥቆ እዚሁ መብላት ሲገባው ሀገሩን ከድቶ ወጥቶ የሚበላ። እኛ ‹ወጥቶ በል ሌባ› ብለነዋል። ‹ነጥቆ ገንቢ ሌባ› ግን አገር ወዳድ ሌባ ነው። እዚሁ ነጥቆ እዚሁ ፎቁንም፣ ፋብሪካውንም፣ ሆቴሉንም፣ እርሻውንም ይገነባል። ለሀገሩም አጥብቆ ያስባል። እዚሁ ነጥቆ እዚሁ የሚሊዮን ብሩን መኪና ያሽቃብጠዋል፤ እዚሁ የመቶ ሺ ብር ውስኪ ያወርዳል።

ነጥቆ ገንቢ ሌባ ደግ ሰው ነው። ሃይማኖተኛ ከሆነ ከነጠቀው ገንዘብ ወይ ለቸርች ወይ ለገዳም ይሰጣል። ነዳያን ያበላል። ድኻ ይረዳል። ሃይማኖተኛ ካልሆነ ደግሞ ለወጣት ማኅበራት ይለግሳል፤ ለቀበሌ ቲሸርት ያሠራል፤ በዓል ስፖንሰር ያደርጋል፤ እንዲህ ያለው ነጥቆ ገንቢ ሌባ ሊበረታታ ይገባዋል። ግን ምን ያደርጋል የሀገራችን ሕግና የኢንቨስትመንት ዐዋጁ በቂ ማበረታቻ ለዚህ ሀገር ወዳድ ሌባ አይሰጥም።

በመጨረሻ የማብራራላችሁ ‹ገፋፊ ሌባና ለካፊ ሌባ› ስለሚባሉት ነው። ገፋፊ ሌባ ማለት ሥጋ ሲበላ አጥንት የማያስቀር፤ እንጀራ ሲበላ ሞሰብ የማይተርፈው፤ ሻይ ሲወስድ ከነ ብርጭቆው፤ የደራሲውን ድርሰት ወስዶ የደራሲውን ስም የሚያጠፋ፤ ሚስቱን መንጠቁ ሳያንሰው ባሏን የሚገል፤ በመሬትህ ላይ ባለ ዘጠኝ ፎቅ ሊሠራ አንተን በዘጠነኛው የኮንዶሚኒየም ፎቅ ላይ የሚወረውርህ፣ ሃምሳ ዓመት የኖርክበትን ቤት ወስዶ ከከተማው ሃምሳ ኪሎ ሜትር አውጥቶ የሚጥልህ ማለት ነው። ለካፊዎቹ ሌቦች ዝም ብለው ነው። እዚህም እዚያም ለኮፍ ለኮፍ ነው የሚያደርጉት።›

ሰውዬው ማብራሪያውን ሲጨርስ አድናቂዎቹ እየሳቁ አጨበጨቡ። ሰው የልቡን ሲነግሩት የኮረኮሩት ያህል ይስቃል ይባል የለ።

‹ታድያ አሁን መፍትሔው ምንድን ነው› አሉ ሰብሳቢው ነገሩ ውስብስብ ብሎባቸው። አንዱ እጁን አወጣ።

‹ለችግሩ መባባስ ዋነኞቹ ተጠያቂዎች ከመሐልና ከታች ያሉት ሌቦች ናቸው። አሁን እኔ ኩሩ ሌባ ነኝ። ልስረቅ አልስረቅ ሰፊው ሕዝብ አያውቅም። እይውልዎት፣ መንደር መንገድ ላይ ያለችውን ዛፍ የሚቆርጠውን እንጂ ደን ውስጥ ያለውን ዛፍ የሚቆርጠውን ማንም አያየውም። አሁን ለኛ ችግር የሆኑብን የመንደር ዛፍ ቆራጮች ናቸው። ለካፊ ሌቦች ከስኳሩም፣ ከጨውም፣ ከድንቹም፣ ከሽማቾቹም ይቀነጣጥቡና ሕዝቡን ያነሣሡታል። ሕዝቡኮ ስኳሩ ወደ ሽማቾች ከገባ በኋላ አለቀ ሲሉት እንጂ መጀመሪያውኑ ወደ ሽማቾች ባልመጣው ስኳር ላይ አይበሳጭም። ሃምሳ ኩንታሉን ወስደን ሃምሳውን ኩንታል ሩብ ሩብ ኪሎ ብናከፋፍለው ‹ተመስገን› ብሎ ነው ወደ ቤቱ የሚሄደው። ሥራው ግልጽነት ያለው እንዲመስል ደግሞ የመጣውን ሃምሳ ኩንታል ከሴቶች፣ ከወጣቶችና ከአዛውንት የተመረጡ ኮሚቴዎችን አሰልፎ እኩል እንዲያካፍሉ ማድረግ ነው።›

‹ልክ ነው።› አለ አንዱ ሰርቆ አደር ኢንቨስተር ‹ሰው መብራት ተቆራረጠብን አለ እንጂ የመብራቱን ኬብል እነማን ናቸው ከውጭ የሚያስገቡት ብሎ ጠየቀ? ዱቄቱ ወደ ሸማቾች በብዛት አልመጣም አለ እንጂ ዱቄቱን እነ እገሌ ብቻ ለምን ከውጭ ያስመጣሉ? ብሎ ጠየቀ፤ አልጠየቀም። ኮንደሚኒየም በትክክል አልደረሰኝም አለ እንጂ እነ እገሌ የከተማ ቦታ በካሬ 300 ሺ ብር የሚጫረቱት ብሩን ከየት ቢያመጡት ነው ብሎ ጠየቀ፤አልጠየቀም። ‹እገሌና እገሌ የተባሉ ዋና አከፋፋዮች ለምን አስወደዱብን፣ ለምን አሳነሱን› አለ እንጂ ‹ግን እነርሱ የውጭ ምንዛሬ ከየት እያገኙ ነው ዕቃውን ከውጭ የሚያመጡት?› ብሎ መች ጠየቀ፤ ስለዚህ ችግሩ እታች ያሉት አቀባባይ ሌቦች አሠራሩን ስላላወቁበት ነው ማለት ነው። አያችሁ ሕዝቡ የዋሕ ነው። በጥፍርህ ስትቧጭረው ‹ጥፍሩን ቁረጡልኝ› ነው የሚለው። ሰውዬውኮ የቧጨረው ጥፍር ስላለው አይደለም። በጥፍሩ እንዲቧጭር የሚያዝ ጭንቅላት ስላለው ነው። ሕዝቡ ‹ጥፍሩን አስቆርጦ› ወደ ቤቱ ይገባል። ለተወሰነ ጊዜ ቧጫሪው ዝም ይላል። ቆይቶ ግን ጥፍሩ ሲያድግ መቧጨሩን ይቀጥላል። መጀመሪያ ጥፍሩን ያሳደገው፤ ተቧጨር ብሎ መብት የሰጠው ማን ሆነና። አሁንም ያስቸገሩን ራሶቹ አይደሉም። ጥፍሮቹ ናቸው።› እንደ ድጓ አድራሽ በሊቃውንት ፊት ዕውቀቱን ያስመሰከረ መስሎት ትከሻውን ሰበቀ።

ሰብሳቢው ግራ እየገባቸውም ቢሆን ‹ሐሳቡን እንጠቅልለው፤ የመቋጫ ሐሳብ አምጡ› አሉ።

ሁለት ሰዎች ተረዳድተው ያዘጋጁትን የአቋም መግለጫ ይዘው ወጡ። እነርሱ የአቋም መግለጫውን ሲያቀርቡ ተሰብሳቢዎቹ ወረቀትና ስክርቢቶ አዘጋጁ።

አንደኛ፡- ኅብረተሰቡ ስርቆትን እንዲጠየፍ ስለ ስርቆት በመገናኛ ብዙኃን ትምህርት ይሰጥ (ይኼ ሲነበብ አንድ አምስቱ በቲቪና ሬዲዮ የሚቀርበውን ማስታወቂያ ለመሥራት እንዴት ከባለ ሥልጣናቱ ጋር እንደሚሠሩ ተንሾካሾኩ፤ አንድ ሁለቱ ደግሞ በእነርሱ ሬዲዮ ጣቢያ ይህን ፕሮግራም ለመሥራት የስፖንሰር ገንዘብ ሲቦጭቁ ታያቸው)

ሁለተኛ፡- በየቀበሌውና በየደረጃው ሕዝቡ ሌቦችን እንዲያጋልጥ ይደረግና ርምጃ ይወሰድ (የተወሰኑት ተሰብሳቢዎች ለቀበሌ ስብሰባዎች ሞንታርቦ፣ ውኃና ኮፍያ ያለ ጨረታ ለማቅረብ ተጠቃቀሱ)

ሦስተኛ፡- ሌብነትን የተመለከተ ዜማ በታዋቂ አርቲስቶች እንዲዘጋጅ ይደረግ (አርት ነክቶናል የሚሉ ነጥቆ አደር አርቲስቶች የሚዘጋጀውን የፀረ ስርቆት ቅስቀሳ ከእነርሱ እንዳይወጣ ዘየዱ)

አራተኛ፡- ስለ ስርቆት አስከፊነት የሚያስተምር ቢል ቦርድ በመላ ሀገሪቱ ይተከል (የማስታወቂያ ድርጅት ያላቸው ተሰብሳቢዎች ይቺ ፕሮጀክት ከኛ አታልፍም ብለው ማሉ) አምስተኛ፡- የፀረ ስርቆት ቀን በየዓመቱ ይከበር። (ቲሸርትና ኮፍያ፣ መድረክና መስተንግዶ የሚያቀርቡ ተሰብሳቢዎች ዓመታዊ ገቢ ተገኘ ብለው ጮቤ ረገጡ።)

ተሰብሳቢዎቹ ሲወጡ የአዳራሹ ዘበኛ በኀዘን ለጓደኛቸው ‹በሬ ሞተና ፍትሐት ሲፈታ ከበሮው ድምጹ እንዳይሰማ ‹ትሽ፣ ትሽ፣ ትሽ› ይል ጀመር። ከዚያ በፊት ‹እድም፣ እድም፣ እድም› ሲል ይሰሙት የነበሩት ጽናጽንና መቋሚያ ‹ምነው ዛሬ ያለወትሮህ ድምጽ እንዳይሰማ ‹ትሽ፣ ትሽ፣ ትሽ› ትል ጀመር› ብለው ቢጠይቁት ‹የሞተው በሬ፤ የሚመታው የበሬ ቆዳ ሆኖብኝኮ ነው። እንዴት ከበሬ ቆዳ ተሠርቼ በሬ ሞተ ብዬ ከበሮ ልምታ› አላቸው ይባላል ብለው ተረቱ። **በዲ/ን ዳንኤል ክብረት**

# መልካም ዜጋ

# ሥነ-ምግባር የተላበሱ መሪዎችና ተቋማት ግንባታ!

ታዋቂው የስራ አመራር ምሁር ፒተር ድሩከር፣ ‘በእድገት ወደ ኋላ ከቀሩ ሀገራት ይልቅ በሥራ-አመራር የተበደሉ ይበዛሉ’ በሚለው አባባሉ በብዛት ይታወሳል፤ አባባሉ ለሀገር ወይም ለድርጅት እድገትም ሆነ ውድቀት ወሳኙ የሰው ሀይል በተለይም መሪዎችና ተቋማት መሆናቸውን ያሳያል፡፡

አስሞለጉ እና ሮቢንሰን why nations fail በሚለው መፅሐፋቸው፣ አንዳንድ ሀገራት መበልፀግ የቻሉት፣ ሌሎች ደግሞ በድህነት አረንቋ የተዘፈቁት በተፈጥሮ፣ በአየር ንብረት፣ በባህል ልዩነቶች ሳይሆን አካታች ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ስርአት በመሪዎቻቸዉ መገንባት በመቻል ወይም ባለመቻላቸው ነው ይላሉ፡፡

በተፈጥሮ ሀብት፣ በአየር ንብረት፣ በባህል መመሳሰል ቢሆን ኖሮ ሰሜን እና ደቡብ ኮሪያ በተመሳሳይ እድገት ላይ በተገኙ ነበር፤ ለልዩነቱ መንስኤ በደቡብ ኮሪያ ፈጠራን የሚያበረታታ ኢኮኖሚና የባለስልጣን የበላይነት ሳይሆን የህግ የበላይነት የሰፈነበት አካታች የፖለቲካ ስርአት በመገንባቱና በአስተማማኝ ሁኔታ ተግባራዊ በመደረጉ ነዉ፡፡ የዚህን አይነት አካታች ስርአት ለመገንባት ደግሞ መሪዎች በተለይም ስነምግባራዊ መሪዎች መኖር ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለዉ፡፡

በስነ-ምግባር አርአያ የሆኑ መሪዎች አካታች ስርአት ይገነባሉ፤ በስነምግባር የዘቀጡ ባለስልጣናት ደግሞ አግላይ ስርአት በመገንባት፣ ሙስናን ባህል በማድረግ፣ ማህበራዊ ካፒታልን በመሸርሸር ሀገርን ወደ ውድቀት አዙሪት ይከታሉ፡፡

በዚህ አለም እንደ ሥነምግባር በመጥፎም ሆነ በጥሩ ለሀገርም ሆነ ለተቋማት ወሳኝ ነገር የለም፤ በአለም ላይ ያደጉ እና የለሙ ሀገራት መሠረታቸው ስነምግባር ነው የሚሉ ወገኖች አሉ፤ በአለም በከፍተኛ ፍጥነት እድገት ያስመዘገቡ የሩቅ ምሥራቅ ኤስያ ሀገራት ደግሞ እድገታቸው ከህዝብ ብሔራዊ መግባባት ጋር ይያያዛል፡፡ እንደ ኮሪያ የመሳሰሉት ሀገራት ሌባ እንኳን ለክቶ የሚሠርቅበት ሀገር ነበሩ፤ ለምሣሌ ለኤክስፖርት በተዘጋጀ ምርትና አገልግሎት ላይ የጉምሩክ ሠራተኞች ስርቆት አይፈፅሙም ነበር፤ መሀንዲሶች በሚገነባው ጤና ጣቢያ፣ ትምህርት ቤት፣ መንገድ የራሳቸውን 10 በመቶ ኮሚሽን ይጨምሩ እንጂ በጥራቱ፣ በጊዜውና በመጠኑ ላይ አይደራደሩም ነበር፡፡

ይህንን እስቲ ከእኛ አገር ሌቦች ጋር አወዳድሩት? ከዚህ በመነሣት ሥነ-ምግባር ሙስናን ለመከላከል ወይም ለመቀነስ ዓይነተኛ ሚና እንዳለው መረዳት እንችላለን፤ ይሁንና በባህል ቢሆን ኖሮ፣ ሰሜን እና ደቡብ ኮሪያ ተመሳሳይ እድገት ላይ በተገኙ ነበር፤ ጥሩ ባህልም የተቋማት ዉጤቶች ናቸዉ፤ ዋናዉ ሁሉንም በእኩል የሚያገለግሉ ተቋማት መገንባት ነዉ፡፡

ማህበረሰቡ ከማንኛውም የመንግሥት ተቋም ፍትሃዊ፣ ቀልጣፋና ትክክለኛ አገልግሎት ይጠብቃል፤ በአሁኑ ጊዜ “ደንበኛ ሁልጊዜ ትክክል ነው፣ ሉአላዊ ነው” የሚሉት አባባሎች ከመቼውም ጊዜ የበለጠ ይሁንታ እያገኙ ነው፤ ደንበኛን ለማርካት የማይጥር ድርጅት፣ ተቋምና ሀገር እራሱን በገመድ አንቆ እንደ መግደል በሚታይበት ወቅት ላይ ደርሰናል፤ ምክንያቱም ደንበኛን /ተገልጋይን/ የሚያማልሉ አገልግሎት ሰጪዎች እንደ አሸን እየፈሉና ድንበር የለሽ እየሆኑ በመምጣታቸው ነው፡፡

ምንም እንኳን ማህበረሰቡ ፍትሀዊና ቀልጣፋ አገልግሎት ቢጠብቅም በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት ግን በተቃራኒው ሥነምግባራዊ እሴቶች በመንግሥት አገልግሎት አሠጣጥ በከፍተኛ ሁኔታ እየተሸረሸሩ ነው፤ ይህ የመንግሥት አገልግሎት አሠጣጥ መላሸቅ በዋነኝነት የሚገለፀው በሙስና መልክ ነው፤ ሙስና የህዝብ ስልጣንን ለግል ጥቅም ወይም ትርፍ ማዋል ነው፡፡



ሙስና ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና አካባቢያዊ ተፅዕኖዎች አሉት፤ በፖለቲካው መስክ ሙስና ለህግ የበላይነትና ለዲሞክራሲ ማበብ ትልቁ እንቅፋት ነው፡፡ ሙስና በተንሠራፋበት የሰዎች እንጂ የህግ የበላይነት የለም፤ የህግ የበላይነት በሌለበት ሁኔታ ተቋማት አይገነቡም፤ ተቋማት ባልተገነቡበት ሁኔታ ደግሞ አካታች ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሥርዓት አይመሠረትም፡፡ በተቋማት ያልታገዘ እድገትና ልማት ዘላቂነት አይኖረውም፡፡

የዳበረ የዲሞክራሲ ባህል ባላቸው ሀገራት ሣይቀር ሙስና፣ የመንግሥት ቢሮዎች፣ ተቋማት፣ መርሆዎች ላይ እምነት በማሣጣት የቅቡልነት ቀውስ ውስጥ ይከታል፤ በማደግ ላይ ባሉ ሀገሮች ደግሞ የበለጠ ጉዳት ያደርሳል፤ ሙስና በተንሠራፋበት ሁኔታ እና ቦታ ተጠያቂነት እና ልጓም ያለው የፖለቲካ አመራር ማስፈን አይቻልም፡፡

በኢኮኖሚው መስክ ሙስና የሀገር ሀብት እንዲወድም ያደርጋል፤ በአብዛኛው ውስን የሆነው የህዝብ ሀብት ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታቸው አነስተኛ ላልሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ግን እጅግ አስደናቂ እና መሰረታዊ ያልሆኑ አገልግሎቶች ላይ እንዲውል ያደርጋል (ለከፍተኛ ሙስና በር ስለሚከፍቱ)፤ ትምህርት ቤት፣ ሆስፒታል፣ መንገድና ውሃ ወደ ገጠር አካባቢ እንዳይስፋፋ ያደርጋል፤ ከሁሉም የከፋው ደግሞ ውድድሩን በመገደብ የነፃ ገበያ እንዳይስፋፋ ያደርጋል፣ ኢንቨስትመንትም ያቀጭጫል፡፡

ሙስና በህብረተሰቡ ማህበራዊ ትስስር ላይ የሚያደርሰው ጉዳት ከሁሉም በላይ ነው፣ ህብረተሰቡ በፖለቲካ ሥርዓቱ ላይ ያለውን እምነት ያቀጭጫል፤ በተቋማትና በፖለቲካ መርሆዎች ላይ ያለውን ተስፋ ያጨልማል፡፡ ይህ ደግሞ በዲሞክራሲ በተመረጡ መሪዎች ሳይቀር ህሊና-ቢስ በማድረግ የህዝቡን ሀብት ወደ ውጭ ሀገር እንዲያሸሹ ይረዳቸዋል፤ ጉቦ መጠየቅ እና መስጠት አፀያፊ ስነ-ምግባር መሆኑ ቀርቶ የተለመደ እና ቅቡልነት ያለው ባህርይ ያደርገዋል፡፡

ስነ-ምግባራዊ መሪ መገንባት ኢትዮጵያ አሁን ለተዘፈቀችበት ብልሹ አሰራርና የሙስና ማእበል ዋነኛው መፍትሄ ነው፤ መሪዎች ስነ-ምግባራዊ ሲሆኑ ተከታዮቻቸዉ ስነምግባራዊ ይሆናሉ፤ መሪዎቹ እና ተከታዮቻቸው ስነምግባራዊ ባህል ይገነባሉ፡፡ ስነምግባራዊ ባህል እንዴት እንደሚገነባ በሚከተሉት ነጥቦች ላይ መረዳት ይቻላል፡-

**ስነ-ምግባራዊ (ግብረ-ገብ) መሪ፡-** መሪ ማለት ተከታይ ያለው ሲሆን መደበኛ ስልጣን ይኑረውም አይኑረውም ተከታይ ካለው መሪ ነው፡፡ ስነ-ምግባራዊ (ግብረ-ገብ) መሪ የሚመራበት መርህ ያለው፣ ለመርሁ የታመነ ትክክል ያልሆነውን እየተወ ትክክል የሆነውን ለመተግበር የሚተጋ፣ እውነተኛና ፍትሀዊ የሆነውን ነገር በመስራት ለተከታዮቹ አርአያ የሚሆን ማለት ነው፡፡ አመራር ሲሆን የጋራ ጥቅምን የሚያራምድና የሚተገብር፣ በማንኛውም የህይወት መመዘኛ ተቀባይነት ያለውንና ተገቢ የሆነውን ነገር የሚፈፅም ነው፡፡

በማንኛውም ጊዜ ድርጊትና አመራሩ ሥነ-ምግባር የተላበሰ ሲሆን ሥነ-ምግባራዊ አመራር ይባላል፤ ስነ-ምግባራዊ ተቋምና መሪ ለመገንባት መርሆዎቹን መከተልና በጥብቅ ተግባራዊ ማድረግን ስለሚጠይቅ በተዋቡና በተሰደሩ ቃላት ተቋማት አይገነቡም፡፡

**የስነምግባራዊ መሪዎች መርሆዎች፡-** የስነ-ምግባራዊ መሪዎች መርሆዎች ከአርስቶትል ጀምሮ ያሉ ናቸው፤ የእነዚህ መርሆዎች ጠቀሜታቸው በተለያዩ ዲሲፕሊን ውስጥ መወያያ መሆናቸው ነው፤ ሥነ-ምግባራዊ መሪ ለመፍጠር መሠረቶች ናቸው፡፡

ሥነ-ምግባራዊ መሪዎች ሌሎችን /ተከታዮቻቸውን/ ያከብራሉ፣ ሌሎችን ያገለግላሉ (The servant-leader is servant first) “መሪ ማለት ተከታይ ያለው ማለት ነው፤ ተከታይ ሳይኖር መሪ መሆን አይቻልም፣ እውነተኛ ተከታይ ለማፍራት ደግሞ እውነተኛ አገልጋይ መሆንን ይጠይቃል” ትክክለኛውን ውሳኔ ይወስናሉ- ይተገብራሉ፣ ሐቀኝነትን (honesty) እዉነትን መናገርን በተግባር ያስመሰክራሉ፣ ማህበረሰብ እና ማህበራዊ ካፒታል ይገነባሉ፣ መሪዎች በቃላቸዉም ሆነ በድርጊታቸዉም አርአያ ይሆናሉ፡፡

**ሥነ-ምግባራዊ ድርጅት እንዴት ይገነባል?** መልካም ስም የአንድ ሀገር ወይም ድርጅት ስኬታማነትንና ውድቀትን ይወስናል፡፡ ለዚህም ነው የአለማችን ቁጥር ሶስት ቢሊየነር ዋረን ቡፌት፤ ‘ከምንም በላይ ለመልካም ስም / Reputation/ ከፍተኛ ትኩረት እሰጣለሁ’ ያሉት፡፡ መልካም ስምን ለመገንባት ብዙ አመታት ይፈጃል፤ ለማፍረስ ግን ጥቂት ሠኮንዶች ይበቃሉ፡፡ ለዚህም ነው ጠንቃቃ ድርጅቶች ለመልካም ስም ከፍተኛ ትኩረት የሚሠጡት፤ መልካም ሥነ-ምግባር ጥሩ ስም እንደሚገነባ ሁሉ መጥፎ ምግባር የሠራተኞችን ሞራል ይጐዳል፣ ወጪን ይጨምራል፡፡ ስለዚህ መልካም ሥነ-ምግባር ለመገንባት ተቋማት ትኩረት እየሰጡ ነው፤ በዚሁ መሠረት ስለ ሥነ-ምግባር ዲዛይን ይሠራሉ፡፡ ሥነ-ምግባራዊ ባህል ለመገንባት ለአራት ጉዳዮች ትኩረት መስጠት እንደሚገባ በቀጣይ ሀሳቦች መረዳት ይቻላል፡፡

**ግልፅ የሥነ-ምግባር እሴቶች መቅረፅ እና መተግበር፡-** እስትራቴጂዎችንና ተግባራትን በአግባቡ፣ በግልፅ መርሆዎች ላይ ተመስርቶ በመቅረፅ በሁሉም ሠራተኞች ዘንድ የጋራ ግንዛቤ ሊያዝ ይገባል፤ ለዚህም ደግሞ በአግባቡ የተቀረፀ ተልዕኮ ያስፈልጋል፡፡ ከመርሆዎች ጋር የተጣጣመ ተልዕኮ መቅረፅ ይገባል፤ የሚቀረፀው ተልዕኮ አጭር፣ ግልፅ፣ ስሜትን የሚያነሳሳና የሚያስተጋባ መሆን አለበት፡፡

ይሁንና የአብዛኞቹን ተቋማት ተልዕኮ በምናይበት ጊዜ በጣም ረጅም፣ ከሠራተኞች የዕለት ተዕለት ተግባራት ጋር ያልተቀናጀና ሠራተኞች ሊመሩባቸው የሚያስችሉ መነሻ አይደሉም፡፡ የተልዕኮ መግለጫዎች በወረቀት ላይ የሚቀመጡ ቃላቶች መሆን የለባቸውም፤ በቅጥር፣ በስንብት፣ በእድገት ወዘተ እንደ ፖሊስ ሆነው ማገልገል አለባቸው፡፡ የአሜሪካ ወታደራዊ ተቋም የሆነውን ፔንታጐን ተልዕኮን በምናይበት ወቅት ምን ያህል ግልፅ፣ አጭርና የሚያነሣሣ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ “Build the best product, cause no unnecessary harm, use business and implement solutions to the environmental crisis’’.

**ሚዛናዊ ፍርድ፡-** ብዙ ሰዎች ውሣኔ በሚወስኑበት ወቅት ሥነ-ምግባርን ግምት ውስጥ የማስገባት ችግር አለባቸው፤ በዚህ የተነሣ ሥነ-ምግባራዊ ጉድለቶች ይከሰታሉ፣ የትኩረት ምንጭም ይሆናሉ፡፡ ለምሣሌ የቅርብ ዘመዳችንን ወይም ጓደኞችንን ስንቀጥር በሌሎች በማናውቃቸው ሰዎች ላይ የምናደርሰውን ጉዳት ግምት ውስጥ አናስገባም፤ አዕምሯችን ያቀበለንን መልዕክት እንደወረደ ተግባር ላይ ስናውል ሚዛናዊ ፍርድ የመስጠት እድላችንን ያጠበዋል፡፡ ስለዚህ ሁልጊዜ ፍርድ ስንሰጥ በምናውቃቻውና በማናውቃቸው መካከል ልዩነት ላለመፍጠር ቢያንስ ሁለት ጊዜ ማሰብ ይገባል፡፡

**ማበረታቻዎች፡-** ግልፅ ተልዕኮን ከመቅረፅ እና ከመተግበር እንዲሁም ሚዛናዊ ፍርድን ከመስጠት ጐን ለጐን መልካም ሥነ-ምግባር የተላበሱ ተቋማትን ለመፍጠር ማበረታቻዎችን ከሥነ-ምግባር ጋር ማያያዝ ይገባል፤ ውጤት የተመዘገበው ስነ-ምግባርን ተላብሶ አገልግሎት በመስጠት ወይም ባለመስጠት መሆኑን ማገናዘብ ያስፈልጋል፤ ሠራተኞች ሥነ-ምግባራዊ ስለሆኑ ማበረታቻ ሊሰጣቸው ይገባል፤ እነዚህ ማበረታቻዎች የተለያዩ ዓይነቶች /ውጫዊ እና ውስጣዊ/ መሆን ይገባቸዋል፡፡

ከገንዘብ ማበረታቻ በተጨማሪ ሠራተኞች የሚያረካቸውን ሥራ በመስራት አዎንታዊ ተፅእኖ ማሣደርን፣ ክብር ማግኘትና መደነቅን ይፈልጋሉ፤ ይሁንና የሥነ-ምግባር አመራሮች ከፋይናንስ ውጭ ያሉ ማበረታቻዎችን ትኩረት ሲሰጧቸው አይታይም፡፡ ስለ እነዚህ ማበረታቻዎች የሚሠጡት ትኩረት አናሣ ነው፣ ይሁንና መልካም ሥነ-ምግባር ለተላበሱ ሠራተኞች እውቅና መስጠትና ማመስገን ይገባል፤ ተሸላሚዎችን የሚሠጣቸውን ሽልማት ለማህበራዊ አገልግሎት እንዲያውሉት ማድረግ የበለጠ ያበረታታቸዋል፤ ሥነ-ምግባራዊ ባህሪ ሥነ-ምግባራዊ ሥራ ብቻ እንዲሠሩ የሚያበረታታ ብቻ ሣይሆን ጥሩ ስሜትም እንዲሰማን የሚያደርግ ነው፡፡

**ባህላዊ ልምዶች፡-** በርካታ ከፍተኛ መሪዎች አስቀድሞ ለተጠቃቀሱት የሥነ-ምግባር መለያዎች ትኩረት ይሰጣሉ፤ ይሁንና ለመካከለኛው አመራር ጥብቅ ሥነ-ምግባራዊ ስታንዳርድ መቅረፅን ችላ ይሉታል፤ በመካከለኛው አመራር የሚቀረፅ የሥነ-ምግባር ስታንዳርድ የሠራተኞችን ባህሪ በማነፅ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳለው ይታመናል፤ ጥሩ መርሆዎች ጥሩ ተከታይ ያፈራሉ፡፡ ሆኖም ሠራተኞች በሚዋሹ፣ በሚያታልሉ፣ በሚሠርቁ መካከለኛ አመራሮች የሚከበቡ ከሆኑ የሚዋሹ፣ የሚያታልሉና የሚሰርቁ የመሆናቸው እድል ከፍተኛ ነው፡፡ ስነምግባራዊ ተቋም የሚገነባዉ በተግባር እንጂ በተዋቡና በተሰደሩ ቃላት አይደለም፡፡

መርሆዎች ስነ-ምግባራዊ ባህልን በማበረታታት ጥሩ ሥራዎች ምን ምን እንደሆኑ ያሣውቃሉ፤ ስለዚህ የሥነ-ምግባር ምልክቶችን /Ethical beacons/ ተግባራዊ ማድረግ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ በአጠቃላይ ስነ-ምግባራዊ መሪዎችንና ድርጅቶችን ለመፍጠር ትኩረት በመስጠት ለሁላችንም የተሻለች ኢትዮጵያን መፍጠር ይገባናል፡፡

**በስንታየሁ ግርማ**